*Ethiop.j.lang.cult.commun.2024, 9(1): 113-142*
*Open Access articles distributed under the License of Creative Common Noncommercial: CC BY 4.0.*
*Copyright© Faculty of Humanities-BDU*
*ISSN: 2518-2919*
https://doi.org/10.20372/ejlcc.v9i1.1757

## Original Research

# ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለው ተፅዕኖ፤ በ 7ኛ ክፍል ተተኳሪነት

**Tsegaye Beyene[1]፣ Mehiret Sadamo[2]፣Abera Hussien[3]**

1የፒ.ኤች.ዲ. ተማሪ ፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ፣ ኢትዮጵያ
2ፒ.ኤች.ዲ.፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ፣ ጂማ ፣ ኢትዮጵያ
3ፒ.ኤች.ዲ.፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ፣ ጂማ ፣ ኢትዮጵያ
**Corresponding author:* tsegabeyene74@gmail.com

## Abstract

This study examined the impact of feedback on students writing skill and motivation. It is a quasi-experimental research and has four groups (three experimental and one control) of students. The study conducted in 2016 E.C. at Haik no.1 primary school and the subjects are 144 grade 7 students. The school and the grade level were selected by simple random sampling and students were assigned in one of the four groups randomly. Pre - post essay writing test and motivation measuring questionnaire were administered to gather the study data. Before the intervention both the experimental and the control groups have taken pre writing test and motivation questionnaire. As a result, there no significance difference among the groups in their writing skill and motivational level. Then all groups practiced the same writing activities for 10 weeks. The only difference among the group during the writing activities is that group one receive written feedback ; group two receive oral feedback , group three revive peer feedback, whereas group four receive no feedback for their essay. Finally, all groups took post writing essay test and motivation questionnaire at the same time. The first question is that does feedback (written, oral and peer) has an effect on student writing skill?. The date analyzed by using one waye anova. The result show that feedback has an effect on students writing skills (F,(3,140)=13.9, p=.000 ). Tukey post hock show that both Oral feedback (m= 32.75, sd= 5.9), and written feedback (m=30.35, sd=6.4) have positive significance effect on students writing skill, While peer feedback has no effect on students writing skill. The second question is that does feedback (written, oral and peer) has an effect on students' motivation?. The analysis show that feedback has an effect (F(3,140) =8.0,p=.000) on students writing motivation. Written feedback (m= 70.4, sd=10.5) and oral feedback (69.8, sd=10.4) have significantly positive impact on students writing motivation, whereas peer feedback has no any effect on writing motivation. Therefore in order to improve students writing skill and motivation, teachers should give constructive written and oral feedback for their students' essay.

*Ethiop.j.lang.cult.com.mun.2024, 9(1): 113-142*
*Open Access articles distributed under the License of Creative Common Noncommercial: CC BY 4.0.*
*Copyright© Faculty of Humanities-BDU*
*ISSN: 2518-2919*
https://doi.org/10.20372/ejlcc.v9i1.1757

## አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ (quasi-experiment) ንድፍን የተከተለ ሲሆን፣ ሶስት የሙከራ ቡድኖች (ሙከራ ቡድን 1፣ ሙከራ ቡድን 2 እና ሙከራ ቡድን 3 ) እና አንድ የቁጥጥር ቡድን (ቡድን 4) ያሉት ባለአራት ቡድን ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2016 ዓ.ም. በሐይቅ ቁጥር1 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ 144 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተመረጠው በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ሲሆን፣ ተማሪዎቹ በዕድል ሰጪ ናሙና ዘዴ ተመርጠው በሙከራና በቁጥጥር ቡድን ተደልድለዋል፡፡ የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና እና 20 የተነሳሽነት መለኪያ ጥያቄዎችን የያዘ የጽሑፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በዚህም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ተመሳሳይ የመጻፍ ተግባር ያከናወኑ ሲሆን፣ ቡድን 1 የጽሑፍ ግብረመልስ፣ ቡድን 2 የቃል ግብረመልስ፣ ቡድን 3 የጥንድ ግብረመልስ እየተሰጣቸው መጻፍን ሂደታዊ በሆነ መንገድ ተለማምደዋል፡፡ በአንጻሩ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የጻፉት አንቀጽ ያለ ምንም የማስተካከያ ግብረመልስ በመደበኛው ዘዴ እየታረመ ተመልሶላቸዋል፡፡ የተገኙት መረጃዎች በነጠላ ናሙና ልይይት (one way anova) ተተንትነዋል፡፡ በዚህም ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ተፅዕኖ እንዳለው (F,3,140=13.9, P=.000) የታወቀ ሲሆን፣ የቃል ግብረመልስ (m= 32.75, sd= 5.9) እና የጽሑፍ ግብረመልስ (m=30.35, sd=6.4) በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ጉልህ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያላቸው መሆኑ በቱኬይ ፖስት ሆክ ተረጋግጧል፡፡ የጥንድ ግብረመልስ ግን በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ምንም ተፅዕኖ እንደሌለው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም፣ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ያለው ሲሆን (F,3,140=8.0, P=.000)፣ የጽሑፍ ግብረመልስ (m=70.4፣ sd= 10.5) እና የቃል ግብረመልስ (m=69.8፣ sd= 10.4) በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳላቸው በቱኬይ ፖስት ሆክ ተረጋግጧል፡፡ በአንጻሩ የጥንድ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ እንደሌለው ጥናቱ አመልክቷል፡፡ በዚህም፣ መምህራን ቀጥተኛ የሆነ የጽሑፍና የቃል የማስተካከያ ግብረመልስ ቢሰጡ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማሻሻል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም፣ ከመምህር የሚሰጥ የጽሑፍና የቃል ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ይጨምራል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፤** ግብረመልስ፣የመጻፍ ተነሳሽነት፣ የመጻፍ ሂደታዊ አቀራረብ፣ የመጻፍ ክሂል

**Citation:** Tsegaye Beyene, Mehiret Sadamo, Abera Hussien. (2024). **ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለው ተፅዕኖ፤ በ 7ኛ ክፍል ተተኳሪነት**. *Ethiopian Journal of Language, Culture and Communication, 9*(1).113-142.
https://doi.org/10.20372/ejlcc.v9i1.1757

| *Submitted: March 2024* | *Revised: May 2024* | *Acceptted: June 2024* |

# 1.መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ የሰው ልጅ መሰረታዊ የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡትና ስሜታቸውን የሚገልጹት በቋንቋ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ከሚያስችሉ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ጽሕፈት ነው፡፡ Sarwat እና ሌሎች (2021) እንደገለጹት የሰው ልጅ በዕድገት ታሪኩ ካዳበራቸው ጉዳዮችና እውቀቱን፣ሀሳቡንና አመለካከቱን ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ከሚያስተላልፍባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ጽሕፈት ነው፡፡ በዚህም እውቀቱም፣ መረጃውን፣ ሀሳቡንና አመለካከቱን ከአንድ ትውልድ ወደቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፈው በጽሕፈት ነው፡፡ ጽሕፈት በታወቀ ስምምነት የቋንቋ ድምጾችን የሚወክሉ ፊደላትን በስርዓት በመቅረጽ ቃላትንና ዓረፍተነገሮችን በመመስረትና ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሀሳባችንንና ስሜታችንን የምናስተላልፍበት ሂደት እንደሆነ Maziane (2019) እና Al- Zyoud እና ሌሎች (2017 ) አስረድተዋል፡፡ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል መጻፍ አንዱ ሲሆን በትምህርትቤት የጽሑፍ ቋንቋን የምናስተምረውም ሀሳብን በጽሑፍ መግለጽ ለግንዛቤና ለትውስታ ከፍ ያለ ሚና ስላለውና እንደማዳመጥ፣ መናገርና ማንበብ ክሂሎች ሁሉ በዕለት ተዕለት መስተጋብራችን ወሳኝ ስለሆነ እንደሆነ Harmer (2001) አስረድተዋል፡፡

በሉላዊነት ዓለም በርካታ ሙያዊ ተግባቦቶች፣ ፕሮፖዛሎች፣ ደብዳቤዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ቃለጉባዔዎች፣ ዘገባዎች፣ ማመልከቻዎች፣ የኢሜል መረጃዎች ወዘተ. የሚከናወኑት በጽሑፍ ነው (Harmer, 2001; Klimova, 2013; Salvaraj እና Aziz, 2019)፡፡ በዚህ ክፍለ ዘመን አብዛኛዎቹ ሙያዎች ጥሩ የመጻፍ ችሎታን የሚጠይቁ በመሆናቸው የመጻፍ ክሂልን ማዳበር አስፈላጊ እንደሆነ Salvaraj እና Aziz (2019) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ተማሪዎች ራሳቸውን በጽሑፍ እንዴት እንደሚገልጹ ካላወቁ በትምህርት ቤት ከመምህሮቻቸው፣ በንግዱ ዓለም ከደንበኞቻቸው፣ በስራው ዓለም ከቀጣሪዎቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከማንኛውም ሰው ጋር መግባባት አይችሉም (Klimova, 2013; Tillema, 2012 & Eggleston, 2017, Andriani & Agustiningsih, 2021)፡፡ ይህም ጽሕፈት ከትምህርት ቤት እስከ ስራ ቦታ በግል ሕይወታችንም ጭምር አስፈላጊ መሆኑንና ይህን ጠቃሚ ክሂል ማዳበር ወሳኝ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው የመጻፍ ክሂል ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነጻጸር በጣም ውስብስብ ክሂል መሆኑን Al-Zyoud እና ሌሎች (2017) እና Wahyuni (2017) ይገልጻሉ፡፡ የተማሪዎችም የመጻፍ ክሂል በጣም አነስተኛ በመሆኑ ቀላል ዓረፍተነገር መመስረትና ተጠየቃዊ አደረጃጀት ያለው ጥሩ አንቀጽ ማዋቀር አይችሉም፤ መጻፍ አንችልም ብለው ስለሚያስቡ ስህተት መስራትንም ይፈራሉ (Andriani & Agustiningsih, 2021)፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል መጻፍ በርካታ እውቀቶችን (የይዘት እውቀት፣ ሀሳብ የማመንጨትና የማደራጀት ችሎታና የጽሕፈት ስምምነት እውቀት) በሌላው በኩል ተገቢ ቃላት የመጠቀም፣ ጥሩ ዓረፍተነገር የማዋቀር፣ ትክክለኛ ሰዋስው የመጠቀም፣ አንቀጽ የመመስረት

ብሎም ሙሉ ድርሰት የመጻፍ ችሎታዎችን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው (Salvaraj & Aziz, 2019; Andriani & Agustiningsih, 2021)፡፡ በመጻፍ ክሂል መከናወን ያለባቸው ንዑሳን ክሂሎች በመኖራቸው አፍ-ፈት ላልሆኑ የሁለተኛ ወይም የውጪ ቋንቋ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን አፍ-ፈት ለሆኑ ተማሪዎችም አስቸጋሪና ፈታኝ ክሂል መሆኑን Kroll (1990) ገልጸዋል፡፡ መጻፍ ክሂለ ብዙ ተግባር እንደሆነ፣ እየጻፉ መማርን እንደሚጠይቅና ወደ ጽሑፍ ከመገባቱ በፊትና ከተገባም በኋላ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ የግድ እንደሚል ማረው(1996) ያስረዳሉ፡፡ Kroll (1994) በበኩላቸው የመጻፍ ተግባር ሂደታዊ እንጂ በአንድ ረቂቅ ተጀምሮ ቀጥ ባለ መስመራዊ ቅደምተከተል ተጽፎ የሚያልቅ አለመሆኑን ገልጸዋል፤ አክለውም መጻፍ ወደኋላና ወደፊት መመላለስን ደጋግሞ ማርቀቅንና መከለስን የሚፈልግ ተግባር መሆኑን አስረድተዋል፡፡

Driver (2012) እና Troia እና ሌሎች (2012) በበኩላቸው መጻፍ በተፈጥሮ የሚዳብር ክሂል ሳይሆን ስልጠናና ልምምድ የሚፈልግ፣ ግላዊ ጥረትን የሚጠይቅና በህግ የሚመራ ስለሆነ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት ስህተት መኖሩ ተፈጥሯዊ ገጽታ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተለይ ለጀማሪ ተማሪዎች መጻፍ ውስብስብና አስቸጋሪ ክሂል ስለሆነ በመጻፍ ሂደት የሚፈጥሩት ስህተት የሚስተካከለው በመምህር ግብረመልስ ነው (Salvaraj & Aziz, 2019; Hidi & Boscolo, 2007)፡፡ የመጻፍ ክሂል አስቸጋሪነት ሀሳብ በማመንጨትና በማደራጀት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ሀሳብን ወደሚነበብ ጽሑፍ በመቀየር ሂደትም የሚያጋጥም ነው፡፡ በመጻፍ ሂደት የሚያጋጥሙ የቃላት፣ የሰዋስው፣ የስርዓተነጥብ፣ የአደረጃጀት ወዘተ. ስህተቶችን ለማስወገድና ተማሪዎች በትክክል እንዲጽፉ፣ ወጥ ስልትን እንዲከተሉ፣ ድግግሞሽን እንዲቀንሱና ሀሳብን በጥንቃቄ እንዲያደራጁ ለማድረግ የግብረመልስ ድጋፍና ማስተካከያ መኖር እንዳለበት Andriani እና Agustinningsih(2021) አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ግብረመልስ መሰረታዊ የሆነ የቋንቋ መማር አካል በመሆኑ በተማሪዎች መማርና ውጤት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ የማስተካከያ ግብረመልስ መስጠት ተማሪ ጸሐፊዎች የጽሑፍ ቅንጫቢዎችን ጥሩ አድርገው እንዲጽፉ የሚረዳ በጣም ጠቃሚ ብልሃት እንደሆነና በጥንቃቄ ከተመረጠና ለተማሪዎች በአግባቡ ከተሰጠ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና የመጻፍ ተነሳሽነት እንደሚያሳድግ የገለጹት Zahida እና Zaru (2014) ናቸው፡፡

Kroll(1990) በበኩላቸው መምህራን የተማሪዎችን የጽሑፍ ጥራት ለማሻሻልና ስህተቶችን ለማረም የተለያዩ የጽሑፍ ማሻሻያ የግብረመልስ ስልቶችን በማቅረብ ጣልቃ መግባት (intervention) እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም የጽሑፍ፣ የቃል፣ የጥንድ፣ የግል፣ በኮምፒዩተር የታገዘ ወዘተ. የመሳሰሉት የግብረመልስ ስልቶች ለጽሑፍ ተግባር በቀጥታ ወይም በኢቀጥታ መንገድ የሚሰጡ ማስተካከያዎች ናቸው፡፡ Kluger እና DeNisi (1996) ደግሞ በተማሪዎች ወቅታዊ አፈጻጸምና በተነደፈው ግብ (ስታንዳርድ) መካከል ያለውን ክፍተት ወይም ልዩነት ለመሙላት ጣልቃ የመግባቱ ስራ ግብረመልስ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

በአለም ዙሪያ መጻፍን መማር ፈታኝ እንደሆነ ሁሉ ተደጋጋሚ፣ ወቅታዊና ትክክለኛ ግብረመልስ አለመስጠትም እንዲሁ መሰረታዊ ችግር መሆኑን Cui (2021) ገልጸዋል፡፡ Akkuzu (2014) ማስተማርን ያለግብረመልስ ማሰብ አካልን ያለ እስትንፋስ፣ ዐጽምን ያለ ስጋና ደም እንደማቆም ይቆጠራል ይላሉ፡፡ ግብረመልስ ስለሰዎች ባህሪ እውነትነትና ሀሰትነት መረጃ የሚሰጥ፣ ተማሪዎች በራሳቸው እይታና በሌሎች እይታ (በመምህራንና በጥንዶች) ስለራሳቸው ለማየት የሚያስችል በር የሚከፍቱበት ነው፡፡ Hattie እና Timperley (2007) እንደገለጹት ግብረመልስ ተማሪዎች ወዴት ነው የምሄደው? እንዴት ነው የምሄደው? እንዲሁም በቀጣይ ምን ይጠበቅብኛል? የሚሉ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን እንዲመልሱና በተሰጣቸው ግብረመልስ ተመስርተው ክለሳና ማሻሻያ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡ Adarkwah (2021) ግብረመልስ ከምዘና ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳለውና የምዘና መሰረታዊ ክፍል እንደሆነ ሲገልጹ፣ Tsagari (2019) ግን፣ የግብረመልስ ሚና ከምዘና በላይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ግብረመልስ የተማሪዎችን ወቅታዊ አፈጻጸም መረጃ በመስጠትና ወደታለመው ግብ በመምራት ምዘናን ከመማር-ማስተማር ጋር ያስተሳስራል፡፡ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማገዝና ጥንካሬና ድክመትን ከመለየት፣ በተማሪዎች ወቅታዊ አፈጻጸምና በሚጠበቀው ግብ መካከል ያለውን ክፍተት ከመሙላትና አማራጭ ስልቶችን ከማቅረብ አንጻር የሂደታዊ ምዘና ግብረመልስ (formative assessment feedback) ተመራጭ እንደሆነ (Adarkwah, 2021) አስረድተዋል፡፡ ይሁንና መምህራን ምዘናን ውጤት ለመመዝገብ እንጂ፣ ከምዘና ተነስተው ግብረመልስ በመስጠት የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል መጠቀም አለመቻላቸው መሰረታዊ ችግር እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ Zahida እና ሌሎች (2013) እንዳሉት ተማሪዎች ከግብረመልስ የተገኙ መረጃዎችን ጽሑፋቸውን ለማሻሻልና ተመሳሳይ ስህተት ላለመድገም ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በመምህርና በጥንድ የሚሰጥ ግብረመልስ (አስተያየቶች፣ጥያቄዎች እና ሀሳቦች) ተማሪው የት ላይ እንደተሳሳተ፣ አላግባብ የሆነ የሀሳብ አደረጃጀት እንዳለ፣ መዳበር ያለበት ሀሳብ እንደቀረና ተገቢ ያልሆኑ ቃላት እንዳሉ ይማርበታል(Rahmawati, 2015; እና Ken, 1990)፡፡

ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻሉ በተጨማሪ፣ ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያግዝ ትምህርታዊ ተግባር መሆኑን Duijnhouwer እና ሌሎች (2010) ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም፤ ግብረመልስ በተማሪዎች አሁናዊ መማርና በተነደፈው ግብ መካከል ያለውን ክፍተት በመሙላት ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ያለው መሆኑን Kluger እና DeNisi (1996) ገልጸዋል፡፡ Andriani እና Agustiningsih (2021) በበኩላቸው ግብረመልስ የተማሪዎችን ተነሳሽነት በማሳደግ የመጻፍ ክሂልን ማሻሻል አላማ ያደረገ ተግባር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ Zahida እና ሌሎች (2014) በበኩላቸው ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ተገቢ ግብረመልስ ስለማያገኙ ለመጻፍ እንደማይነሳሱ ገልጸዋል፡፡ ለመጻፍ ተነሳሽነት ስለሌላቸውም ፍርሃት ያድርባቸውና የመጻፍ ብቃታቸውም ዝቅተኛ ይሆናል፡፡

Hidi እና Boscolo(2007) እንደገለጹት የቋንቋ መምህራን ተነሳሽነትን በሚመለከት የጽሕፈት ተመራማሪዎችን የሚጠይቋቸው ኹለት መሰረታዊ

ጥያቄዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ለምን የላቸውም? ኹለተኛው የመጻፍ ተነሳሽነታቸው የሚጨምረው እንዴት ነው የሚሉት ናቸው? እነዚህ ጥያቄዎች በአንድ በኩል ተማሪዎች ለመጻፍ ተነሳሽነት እንደሌላቸው የሚጠቁሙ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸውን ዝቅተኛ ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ስልቶች ምን እንደሆኑ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ Ellis (2009)ን ጠቅሰው Hizwari እና Hamidun (2013) እንደገለጹት ግብረመልስ ተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ ብሎም ስነልሳናዊ ትክክለኛነትን በማረጋገጥ ተነሳስተው ጥሩ ጽሑፍ እንዲጽፉና ሀሳባቸውን እንዲያስፋፉ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በተጨማሪም፤ ተማሪዎችን በመደገፍ (scaffold) ለቋንቋ ትምህርት በተለይ ደግሞ ለመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ግብረመልስ ወሳኝ ዘዴ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ ግብረመልስ በተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ንድፈሀሳቦችና ጥናቶች ይደግፋሉ (Shunk, 1995)፡፡ በተነሳሽነት ላይ በሚኖረው ተጽዕኖ የተነሳም በመጻፍ አፈጻጸም ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ግብረመልስን በአዎንታዊ የሚቀበሉ ተማሪዎች ፈታኝ ሁኔታዎችን ተቋቁመው ተግባራትን ለማከናወን ከፍተኛ ተነሳሽነት አላቸው፡፡ በዚህም ተነሳሽነታቸውን ይዘው ውጤታማ ለመሆን ጠንክረው ይሰራሉ፡፡ ይሁንና የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታም ሆነ ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ጽሑፍ፣ ከኢንተርንሺፕ ምልከታና ከመምህራን ውይይት ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቋንቋ መምህራን የመጻፍ ተግባር አድካሚ ነው በሚል ተማሪዎች እንዲጽፉ አያበረታቱም፡፡ በዚህም፣ መምህራን በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የጽሑፍ ችሎታ የሚያሻሽል ተግባርና ያንን ተግባር ተከትሎ ገንቢ የሆነ ተጨባጭ ግብረመልስ ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ተማሪዎችም መጻፍን የሚፈሩ፣ አቀናብረው ሳይሆን የተጻፈውን ብቻ የሚገለብጡና ጽሑፎቻቸውም ቢሆኑ ለማንበብ እጅግ ፈታኝ የሆኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ ይህ ጥናት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻልና ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሳደግ በሚያስችሉ ግብረመልሶች ፍተሻ ላይ ያተኩራል፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

መጻፍ ለመግባባት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ለማገልገል፣ ዕውቀት ለማግኘትና የተማሩትንም መልሶ ለማንጸባረቅ የሚያስችል መሰረታዊ ክሂል ቢሆንም፣ የበርካታ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል አሳሳቢ ችግር ውስጥ መውደቁን የተለያዩ ሀገራት ጥናቶችን በመጠቅስ Rietdijk እና ሌሎች (2018) አስረድተዋል፡፡ በአሜሪካ national Assessment for education progress (NAEP) እንዳረጋገጠው አንድ አምስተኛ የሚሆኑ የስምተኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከመሰረታዊ የመጻፍ ደረጃ በታች ውጤት አምጥተዋል፡፡ በእንግሊዝም በርካታ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ከሚጠበቀው የመጻፍ ብቃት በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በፖርቹጋል ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ደካማ ጸሐፊዎች ናቸው፡፡ በጀርመንም አንድ ሶስተኛ የሚሆኑ የዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች ተቀባይነት የሌለው ቴክስት እንደሚጽፉ ተረጋግጧል፡፡ በኔዘርላንድም ተመሳሳይ ችግር መኖሩን በተማሪዎች የመጻፍ አፈጻጸም ላይ የተካሄዱ ጥናቶች አሳይተዋል፡፡ በደች የተካሄዱ ሁለት ጥናቶችም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ (11-12 ዓመት) ተማሪዎች የሚጽፉት ጽሑፍ ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከስልትና ከተግባቦት ብቃት አኳያ አስከፊ ጉድለት(flaw) ያለበት መሆኑን አሳይተዋል፡፡ በአጠቃላይ Rietdijk እና ሌሎች (2018) እንዳሉት ይህ የተለያዩ ሀገራት ንጽጽር የሚያሳየው የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ችግሩ የጋራ መሆኑንና የበርካታ ሀገራት የመጻፍ ክሂል ትምህርት መሻሻል የሚያስፈልገው መሆኑን ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም፣ Duijnhouwer እና ሌሎች (2010) እንዳስረዱት ከመጻፍ ክሂል አስቸጋሪነትና ውስብስብነት ባህሪ የተነሳ በርካታ ጀማሪም ሆኑ ተመራቂ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው ከበቂ በታች ነው፡፡ ማረው (1996) በበኩላቸው በዲፕሎማም ሆነ በዲግሪ ደረጃ በአማርኛ ቋንቋና መሰል ትምህርት ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ብዙ ተማሪዎች ትልቁ ችግራቸው በቋንቋቸው መጻፍ አለመቻል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በበርካታ ትምህርት ቤቶች ከተደረጉ ምልከታዎች መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች አፋቸውን በፈቱበትና አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚማሩበት አማርኛ ቋንቋ የተሟላ ዓረፍተነገር መመስረትም ሆነ ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ይቸግራቸዋል፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚ ለኮሌጅ-ትምህርትቤት ግንኙነት(school-college link)፣ ለኢንተርንሺፕና ለፕራክቲከም ምልከታዎች ወደተለያዩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሄደበት ወቅት የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በተስተካከሉ ዓረፍተነገሮች አንቀጽ መጻፍ እንደማይችሉ ለማየት ችሏል፡፡ መጻፍን በአግባቡ ስላልተለማመዱ ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከባድ ችግር ሆኗል፡፡ ከእውነተኛ የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደት ምልከታ ለመረዳት እንደተቻለው የመጻፍ ተግባር በተመደበለት ክፍለ ጊዜ ልክ እየተተገበረ አይደለም፡፡ የተለያዩ ግብረመልሶችን በመስጠት ተማሪዎች የመጻፍ ድርሰት እንዲከልሱና እንዲያሻሽሉ ማድረግ አድካሚና አሰልቺ ተደርጎ በመወሰዱ መምህራን በውል ሲተገብሩት አልታዩም፡፡ በዚህም ተማሪዎች የተሟላ መልዕክት የሚያስተላልፍ፣ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ አወቃቀር ያለው፣ በተገቢ ቃላት የተጻፈና አስፈላጊ ስርዓተነጥቦችን የያዘ ጽሑፍ መጻፍ አይችሉም፡፡ ጽሑፋቸውም ቢሆን ለማንበብ እጅግ ፈታኝ የሆነ ነው፡፡ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ከተደረጉ ኢመደበኛ ውይይቶች መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች የተሟላ ሀሳብ ያለው አንቀጽ ቀርቶ የተስተካከለ ዓረፍተነገር የመመስረት ችግር አለባቸው፡፡ ስለሆነም የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የመጻፍ ችግር አሁንም የቀጠለ በመሆኑ በትምህርት ጥራትና በተማሪዎች መማር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ዝቅተኛ መሆን ምክንያቱ የመጻፍ ትምህርትን በክፍል ውስጥ በተገቢ ሁኔታ አለመተግበር፣ ለመጻፍ ሂደቶች ምንም ትኩረት አለመስጠትና ወይም ትንሽ ትኩረት መስጠትና ተማሪዎች ለጻፉት ጽሑፍ በቂ ግብረመልስ አለማግኘት መሰረታዊ ችግሮች መሆናቸውን Rietdijk እና ሌሎች

(2018) አስረድተዋል፡፡ Sarwat እና ሌሎች (2021) ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል አነስተኛ መሆኑን ገልፀው ለዚህም ምክንያቶቹ የተማሪዎች ተነሳሽነት አለመኖር፣ ለመጻፍ በቂ ጊዜ ማጣት፣ የማንበብና የመጻፍ ልምድ ማነስ፣ ለጻፉት ጽሑፍ ተገቢ ግብረመልስና አስተያየት አለማግኘት፣ የቁሳቁስ እጥረት፣ የክፍለጊዜ መጨናነቅና የተማሪዎች ማህበራዊ ዳራ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል በዚህ ጥናት ሊተኮርባቸው የታሰቡት የተማሪዎች ለመጻፍ ተነሳሽነት አለመኖርና ለጻፉት ጽሑፍ ተገቢ ግብረመልስና አስተያየት አለማግኘት ናቸው፡፡ ምክንያቱም አጥኚው በማስተማር ሂደት ባደረጋቸው ምልከታዎችም ሆነ አንደኛ ደረጃ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ባካሄዳቸው ውይይቶች እንደተረዳው ተማሪዎች የመጻፍ ተግባር ሲሰጣቸው ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ መምህራንም የመጻፍ ተግባር አድካሚ ነው በሚል እሳቤ ለተማሪዎች የመጻፍ ተግባርና ተገቢ ግብረመልስ እንደማይሰጡ ተመልክቷል፡፡ ይህን ሀሳብ ለማጠናከር መጻፍ ለዘለቂ የትምህርት ስኬት መሰረት ቢሆንም፣ መምህራን መጻፍን የሚያስተምሩበትና ለተማሪዎች ጽሑፍ ግብረመልስ የሚሰጡበት ስልት ችግር ያለበት መሆኑን Kalipa (2014) ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ለተማሪዎች የመጻፍ ብቃት (performance) ዝቅተኛ መሆን ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ Yuk እና Yunus (2021) ገልጸዋል፡፡ የመጀመሪያው፤ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መሻሻል አስተያየትና ገንቢ ግብረመልስ በመስጠት በኩል የመምህራን ድርሻ አነስተኛ መሆን ሲሆን፣ ሁለተኛው ለመጻፍ ሂደት ወሳኝ የሆነው የቅድመመጻፍ ሂደት አለመተግበር ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች ዝቅተኛ የመጻፍ ብቃት እንዳላቸው አስረድተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ዝቅተኛ መሆንና ለመጻፍ ተነሳሽነት መቀነስ የመምህራን ተገቢ ግብረመልስ አለመኖር መሆን አለመሆኑ እና ተገቢ ግብረመልስ መስጠት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ያሻሽል እንደሆነ መመርመር የዚህ ጥናት አንደኛው ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

በአለም ዙሪያ በግብረመልስ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ግብረመልስ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል በሚኖረው ሚና ላይ እኩል አዎንታዊ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ልዩነት ያመጣል? ከሆነስ የትኛው ግብረመልስ? በየትኛው ዘርፍ ላይ? የመምህር፣ የጥንድ፣ የቃል፣ የጽሑፍ ግብረመልስ ወይስ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግብረመልስ? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ልዩነቶች ታይተዋል (Hyland & Hyland, 2006)፡፡ ይህ ማለት ከጥናቶቹ ልዩነት አይጠበቅም ወይም ተመሳሳይ ውጤት ይኑራቸው ለማለት ሳይሆን በዘርፉ የሚካሄደው ጥናት መቀጠሉን ለማሳየት ነው፡፡ በዚህም የትኛው የግብረመልስ ስልት የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ለማሻሻል የበለጠ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ተጨማሪ ምርምሮች እንደሚያስፈልጉ ጥናቶቹ ጠቁመዋል (Ferris, 2003)፡፡ በዚህም መሰረት፣ ይህ ጥናት የተለያዩ የግብረመልስ ስልቶች በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው ለመመርመር የታለመ ጥናት ነው፡፡ ስለሆነም፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት በማሻሻል ረገድ

ከጽሑፍ፣ ከቃልና ከጥንድ ግብረመልሶች የትኛው የተሻለ ተፅዕኖ እንዳለው መፈተሽ የዚህ ጥናት ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

ከግብረመልስ ጋር በተገናኘ በአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ድግሪ ሰለሞን (1987) የብጤ ዕርማት፣ ትዕግስት (1998) የመምህር ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ፣ እንዳለ (1992) የመምህር ጽሑፋዊ ግብረመልስ፣ በሶስተኛ ድግሪ ዳዊት(2008) የመምህር-ተማሪ ምክክርና የመምህር ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚል በመጻፍ ላይ ያጠኑት ጥናት ግብረመልስ የተማሪዎችን ጽሑፍ ለማሻሻል ያለውን ድጋፍ ለመፈተሽ እንጂ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት ዕምነትና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለማጥናት ያለመ አይደለም፡፡ በተጨማሪም፤ እነዚህ ጥናቶች በኹለተኛ ደረጃ፣ በመሰናዶና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተካሄዱ በመሆናቸው አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያለውን የመጻፍ ችግር አላጠኑም፡፡ በመሆኑም፤ይህ ጥናት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል፣ የግለብቃት ዕምነትና የተነሳሽነት ችግር የተለያዩ የግብረመልስ ምርጫዎችን በመተግበር ይፈታ እንደሆነ ማጥናት ሶስተኛው አነሳሽ ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡

በአጠቃላይ፣ ከላይ የቀረቡት ክፍተቶች ማለትም የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችግር አሁንም ድረስ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ያልተፈታ ችግር የመሆኑ ምክንያት ምናልባት ተገቢ የመምህራን የግብረመልስ አለመኖር መሆን አለመሆኑን መፈተሽ፣ የግብረመልስ ምርጫ በመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ የፈተሹ ጥናቶች በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ መጻፍ ክሂል ላይ አለመኖራቸው፣ የጥናት ክፍተት መኖሩና የውጪው ዓለም ጥናት ውጤቶች ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ለማሻሻል ባለው ተጽዕኖ ላይ ተጨማሪ ጥናቶችን ማካሄድ እንደሚያስፈልግ መጠቆማቸው ለዚህ ጥናት መከናወን እንደአነሳሽ ምክንያት ተወስደዋል፡፡ ከላይ የቀረቡትን አነሳሽ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

1. ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ተፅዕኖ አለው?
2. ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ አለው?

# 2.ክለሳ ድርሳናት

## 2.1.የጥናቱ ንድፈ ሀሳቦች (Theories)

በርካታ ንድፈ ሀሳቦችና የምርምር ‹‹ፓራዳይሞች›› የግብረመልስን ጽንሰሀሳብ ማዕካላዊ ጉዳያቸው አድርገው ትንታኔዎችን እንዳቀረቡ Kluger እና DeNisi (1996) ገልጸዋል፡፡ በግብ መንደፍ ንድፈ ሀሳብ (Goal setting theory) ግብረመልስ በተቀመጠው ግብና በተማሪዎች አሁናዊ አፈጻጸም መካከል ጣልቃ

በመግባት ተማሪዎች ከግብ አንጻር ማስተካከያዎችን እንዲያደርጉ መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ በባህሪያውያን ንድፈሀሳብ (behaviorist theory) ግብረመልስ ተማሪዎች ከመምህራቸው ለሚሰጣቸው ቀስቃሽ የሚሰጡት ምላሽ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ማበረታቻ (reinforcement) ወይም ቅጣት (punishment) ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል የአዕምሯውያን ንድፈሀሳብ (Cognitive theory) ለአዕምሯዊ ሂደት እንጂ በውጫዊ አካል ለሚሰጥ ማበረታቻ ብዙም ትኩረት የማይሰጥ ንድፈሀሳብ ሆኖ ታይቷል፡፡ በዚህ ንድፈሀሳብ የመምህራን ሚና ተማሪዎች በራሳቸው ንቁ ተሳትፎ ሲማሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ Flower እና Hayes (1981) እንዲሁም Salvaraj እና Aziz (2019) ገልጸዋል፡፡

ሌላው ንድፈ ሀሳብ የማህበረ-ባህላዊ (socio-cultral theory) ንድፈሀሳብ ሲሆን፣ የዚህ ንድፈሀሳብ ዋና ተፅዕኖ ፈጣሪ Vygotsky ነው (Nurfaidah, 2018; Daffern & Mackenzie, 2020)፡፡ ይህ ንድፈሀሳብ ለመማር መሰረቱ ባህልና ማህበረሰብ መሆኑ ላይ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን፣ የተማሪዎች መማር ላቅ ያለ እውቀት ባላቸው የአካባቢ ሰዎች ይደገፋል፡፡ በዚህ ንድፈሀሳብ የእድገት ሽግግር ዞን (Zone of proximal development)፣ ድጋፍ (scaffolding) እና ጣልቃ መግባት (intervention) ቁልፍ ጽንሰሀሳቦች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ Zubaidi (2015) እንዳስረዱት በማህበረ-ባህላዊ ንድፈሀሳብ መሰረት ህጻናት የማህበራዊ ተራክቦ ውጤት ናቸው:: ምክንያቱ ደግሞ በማህበረ-ባህላዊ እሳቤ በሌሎች መታገዝ፣ መስተጋብር መፍጠርና ማህበረ-ባህላዊ አውድ መኖር ለመማር መሰረታዊ ጉዳዮች ስለሆኑ ነው፡፡ እንደዚሁም Nurfaidah (2018) መማር በህጻናትና በታላላቆቻቸው መካከል በሚደረግ መስተጋብር ቅርጽ እንደሚይዝ ገልጸዋል፡፡

ይህ ንድፈሀሳብ ከሌሎች ንድፈሀሳቦች በተለየ ሁኔታ ዕውቀት ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከመምህርና ከጥንድ ጋር በሚደረግ መስተጋብርና ዕገዛ ይገነባል፤ ከአዋቂዎችና ከአቻዎች ጋር የሚደረገው መስተጋብር ደግሞ አዕምሯዊ እድገትን እንደሚጨምር panahi እና ሌሎች (2013) ያስረዳሉ፡፡ Hyland (1990) እና Ferris (1995) እንዳብራሩት ግብረመልስ ተከታታይ፣ ሂደታዊና መስተጋብራዊ ሲሆን፣ ከመምህር ብቻ ሳይሆን ከጥንድ፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ በውጤት፣ በአስተያየት፣ ስህተት በማረም፣ በጥንድ ክለሳ፣ በማማከር፣ በውይይት በግለምዘና መልክ የሚሰጥ ነው፡፡ ስለሆነም፣ በዚህ ጥናት ውስጥ የማህበረ-ባህላውያን ንድፈሀሳብ ጉልህ ድርሻ የሚኖረው ተማሪዎች ከእነሱ ላቅ ያለ እውቀት ባላቸው ሰዎች (teachers & peers) ድጋፍ ሲደረግላቸው ከፍ ወዳለ የእድገት ደረጃ ይሸጋገራሉ የሚል መሰረታዊ ነጥብ ስላለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ለሚጽፉት የተለያየ ረቂቅ ከመምህርና ከጥንድ በሚሰጣቸው የቃል፣ የጽሑፍና የጥንድ ግብረመልስ የተሻለ የጽሑፍ ክሂል ላይ ይደርሳሉ ከሚለው ሀሳብ ጋር ይገናኛል፡፡

## 2.2.ግብረመልስ

*ግብረመልስ ከአንባቢ ለጸሐፊ የሚሰጥ መረጃ ወይም ግብዓት ሲሆን፣ ስለተማሪዎች ጽሕፈት ድክመትና ጥንካሬ የመረጃ ምንጭና ተማሪዎች ስለሚያደርጉት ማሻሻያ መንገርና መምራት እንደሆነ የገለጹት* Elashri (2013)፣ Wahyuni (2017) *እና* Ken(1990) *ናቸው።* Driver (2021) *እንዳብራሩት ደግሞ የማስተካከያ ግብረመልስ ተማሪዎች በጽሑፍ ውስጥ ለሰሩት ስህተት በመምህራን፣ በባለሙያዎች ወይም በጥንዶች በመጀመሪያ ቋንቋ፣ በሁለተኛ ቋንቋ፣ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በኮምፒውተር፣ የሚሰጥ አጸፋዊ ምላሽ ነው። ግብረመልስ ስለትምህርት አፈጻጸማቸው በአብዛኛው መሻሻልን አላማ አድርጎ ለተማሪዎች የሚሰጥ መረጃ መሆኑን* Ur(1996) *አስረድተዋል።* Panadero *እና ሌሎች* (2018) *የተለያዩ ምሁራን የሰጧቸውን የግብረመልስ ብያኔዎች ዘርዝረዋል። ግብረመልስ አሁን ባለውና በሚጠበቀው ደረጃ መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚሰጥ መረጃ ነው፤ ግብረመልስ የተማሪዎች ትምህርታዊ ምላሽ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን የመግለጽ ሂደት ነው፤ ግብረመልስ አንድ ስራ እንዴት ውጤታማ ሆኖ እንደተሰራ ወይም እንደሚሰራ የሚሰጥ መረጃ ነው፤ ግብረመልስ የአንድን ሰው አፈጻጸም በሚመለከት ከውጫዊ አካል የሚሰጥ መረጃ ነው። ግብረመልስ ከተቀመጡ ግቦችና ደረጃዎች አኳያ ስለተማሪዎች ወቅታዊ መማር የሚሰጥ መረጃ እንደሆነ ገልጸዋል።*

*የግብረመልስ ዋነኛ አላማ በተማሪዎች ወቅታዊ አፈጻጸም፣ ግንዛቤና በሚጠበቀው ግብ መካከል ያሉ ልዩነቶችን* (gaps) *መቀነስ ነው። እነዚህን ልዩነቶች ለማጥበብ መምህራንና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ስልቶች አነሰም በዛም መማርን ያፋጥናሉ ተብሎ ይጠበቃል* (Hattie and Timperley, 2007)። *በማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ግብረመልስ የመጻፍ ሂደታዊ አቀራረብ መሰረታዊ አላባ ስለሆነ የቋንቋ ክሂሎችን ለመማር ትልቅ ሚና ይጫወታል* (Saito & Zhang, 2012 & Rahmawati, 2015)። Elashri (2013) *እንዲሁም* Razali *እና* Juperi(2016) *እንደገለጹት ደግሞ ግብረመልስ በተማሪዎች የጽሑፍ ሥራ ላይ የሚሰጥ አስተያየት፣ ጥያቄና የስህተት ማስተካከያ በመሆኑ ተማሪዎች የጽሑፍ ቋንቋቸውን እንዴት እያሻሻሉ እንደሆነ ጥሩ አመላካች ሲሆን፣ መምህራንም ተማሪዎቻቸው የሚቸገሩበትን ቦታ እንዲለዩና እንዲመዝኑ ይረዳቸዋል። ግብረመልስ ተማሪዎች ምን ጥሩ እንደሰሩና አሁንም ምን ማሻሻል እንዳለባቸው ያሳያቸዋል፤ ለቀጣዩ ስራም ለመዘጋጀት ያግዛቸዋል።* Elashri (2013)፣ Mi (2009)፣ Littleton (2011) *እና* Getchell (2011)*ን ዋቢ አድርገው እንዳስረዱት በአጠቃላይ ግብረመልስ ለተማሪዎች ሶስት መሰረታዊ ጠቀሜታዎች ይሰጣል። የመጀመሪያው፣ ተማሪዎች የጽሑፍ አፈጻጸማቸው ጥሩ መሆን አለመሆኑን ይለዩበታል። ሁለተኛው፣ ጥሩ አፈጻጸም የሌላቸው እንደሆነ የማስተካከያ ርምጃ እንዲወስዱና እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል። ሶስተኛው ደግሞ፣ ግብረመልስ ጽሑፋቸውን እንዲያሻሽሉ ብቻ ሳይሆን በሌላ አቅጣጫ እንዲያዩ የእይታ መነጽራቸውን እንዲቀይሩ ይረዳቸዋል።*

Zahida እና ሌሎች (2014) እና Driver (2021) ግብረመልስ አይነቱ ብዙና የተለያየ ስለሆነ ተመራማሪዎች ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር እንደሚከፍሉት አስረድተዋል፡፡ በዚህም ግብረመልስ ከሰጪ አንጻር (የመምህር፣ የጥንድ፣ የግል፣ የኮምፒውተር)፣ ከጊዜ አኳያ (የወዲያው፣ የዘላቂ)፣ ከቅርጽ አንጻር (ቀጥተኛ፣ ኢቀጥተኛ)፣ ከማቅረቢያ ስልት አኳያ (የጽሑፍ፣ የቃል) እንዲሁም ከግብረመልሱ ትኩረት አኳያ (ቅርጽ ተኮር፣ ይዘት ተኮር) ተብሎ ይከፋፈላል፡፡ Elshirbini (2013) በበኩላቸው ግብረመልስን የመምህር፣ የጥንድ፣ የቃል፣ የጽሑፍ፣ ይዘት ተኮር፣ ቅርጽ ተኮር፣ ኮምፒውተር ተኮር፣ ቀጥተኛ፣ ኢቀጥተኛ በማለት ከፍለውታል፡፡ እንዲሁም Mubarak (2013) ግብረመልስን የጽሑፍ ማስተካከያ (ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ)፣ አስተካክሎና ደግሞ መጻፍ (reformulation)፣ የመምህር-ተማሪ ኮንፈረንስ፣ የጥንድ ግብረመልስና የኮምፒውተር አገዝ ግብረመልስ (CALL) በማለት በአምስት ከፍለውታል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን የግብረመልስ ዘርፎች ሁሉ በአንድ ጊዜ ማጥናት እጅግ ሰፊ ስለሚሆን ለጥናት እንዲያመችና ፋይዳቸውንም ለይቶ ለማመልከት በተወሰኑት የግብረመልስ አይነቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ጥናት የሚያተኩርባቸው የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ ግብረመልሶች ናቸው፡፡

የጽሑፍ ግብረመልስ መምህራን የተማሪዎችን ጽሑፍ አንብበው ቀጥተኛ/ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ስህተቶቹን በመለየት፣ በማስመርና በማክበብ በይዘቱና በአደረጃጀቱ ላይ ማስተካከያ ጽፈው የሚሰጡበት ሂደት ነው፡፡ Ken(1990) እንዳስረዱት በአብዛኛው መምህራን የተማሪዎች የጽሑፍ ሥራ ላይ አስተያየቶችን/ግብረመልሶችን የሚሰጡት በመጻፍ ነው፡፡ የጽሑፍ ግብረመልስ የተለመደ ቢሆንም ውይይት ስለማይደረግበትና ተማሪዎች የመምህራንን ጽሑፍ ላይረዱት ስለሚችሉ ሁልጊዜ ውጤታማ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል የቃል ግብረመልስ በግብረመልስ ሰጪው (በመምህር) እና በግብረመልስ ተቀባዩ(ተማሪ) መካከል የሚከናወን ቃላዊ መስተጋብር ነው (Ashrafi et al., 2018)፡፡ የቃል ግብረመልስ የፊት ለፊት ኮንፈረንስ እየተባለም ይጠራል፡፡ በቃል ግብረመልስ ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር ስለጽሑፋቸው በቃል እንዲወያዩ ዕድል ይሰጣል (Hyland, 2003):: በዚህ ጥናት የሚተኮርበት ሶስተኛው የግብረመልስ አይነት የጥንድ ግብረመልስ ነው፡፡ የጥንድ ግብረመልስ የጥንድ ምላሽ፣ የጥንድ አርትኦት፣ የጥንድ ሂስ፣ የጥንድ ግምገማ በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል (ken,1990; Razali & Jupri 2014)፡፡ የጥንድ ግብረመልስ ሰፊ የሆነ ሀሳብ የሚገኝበት፣ ከመምህር ግብረመልስ ጋር ሲነጻጸር ተማሪዎችን ፍርሃት ውስጥ የማይከትና ነጻነት የሚሰጥ መሆኑን cui (2021) ይገልጻሉ፡፡ የጥንድ ግብረመልስ ድክመቶች ቢኖሩበትም፣ አሁንም ድረስ በርካታ መምህራንና የኮርስ አዘጋጆች እያካተቱት ያለ ታዋቂ ግብረመልስ ነው (Hyland & Hyland, 2006)፡፡ በአጠቃላይ የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ ግብረመልስ ምርጫዎች በመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ በዚህ ጥናት ውስጥ ቀርቧል፡፡

## 2.3.የመጻፍ ክሂል

ተማሪዎች ሀሳባቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ክንዋኔዎችን፣ እውነታዎችን ወዘተ. በጽሑፍ መግለጽ የሚችሉት እንዴት እንደሚጽፉ ሲማሩ ነው፡፡ መጻፍ ለመጀመሪያ ቋንቋ ጸሐፊዎችም ይሁን ለሁለተኛና ለውጪ ቋንቋ ጸሐፊዎች አስቸጋሪ ውስብስብ ክሂል ስለሆነ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን መማርና ማዳበር አለባቸው፡፡ ለዚህም በማንኛውም የመጻፍ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ አቀራረቦች ወሳኝ ተደርገው ይወሰደሉ፡፡ በsalvaraj እና Aziz (2019) ገለጻ መሰረት የቋንቋ መምህራን ለአንድ የተወሰነ የመጻፍ ትምህርት የሚሆኑ የመጻፍ አቀራረቦችን መወሰን የሚጠበቅባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ የመጀመሪያው በመጻፍ ትምህርት ውስጥ ተገቢ አቀራረብን መለየት ስኬታማ ውጤት ለማየት መሰረት ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተገቢ ያልሆነ የመጻፍ አቀራረብ መጠቀም መምህራንና ተማሪዎች ከብዙ የጽሑፍ ስራ በኋላ እንዲበሳጩና ተነሳሽነታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ መምህራን ከነደፉት የመጻፍ ግብ አንጻር ተስማሚ የመጻፍ አቀራረብ መጠቀም ጠቀሜታ ስላለው ነው፡፡

ስለሆነም የመጻፍ አቀራረብን ሳይወስኑ ወደመጻፍ ተግባር መግባት የመጻፍ ትምህርቱ ወደብዙ አቅጣጫ እንዲበታተንና የታለመው የመጻፍ ግብም ሳይሳካ እንዲቀር ያደርጋል፡፡ በsalvaraj እና Aziz (2019) የተጠቀሱት Scott (1996) እንዳብራሩት የመጻፍ ግብን ለማሳካት የመጻፍ አቀራረብን ወስኖ መጻፍ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎችን ለተለያዩ የመጻፍ አቀራረቦች ማጋለጥ ለወደፊት ጽሑፋቸው ከመጻፍ አላማቸው አኳያ ትክክለኛ አቀራረብን ለይተው እንዲጠቀሙ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ በዚህም መጻፍን በክፍል ውስጥ ለማስተማር ጥቅም ላይ የሚውሉና በብዙ ምሁራን ዘንድ የሚጠቀሱ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች ውጤት ተኮር አቀራረብ፣ ዘውግ ተኮር አቀራረብ፣ ሂደት ተኮር አቀራረብና ሂደተ-ዘውግ አቀራረብ ናቸው (Maryam, 2017) ፡፡

ውጤት ተኮር አቀራረብ (product Approach) በቅርጽና በስነልሳን እውቀት ላይ የሚያተኩር ጥንታዊ አቀራረብ ሲሆን መጻፍ ማለት የስነልሳን (የቃላትና የመዋቅር) እውቀት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ አቀራረብ ተጽፎ በተጠናቀቀው የጽሑፍ ስራ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ተማሪዎች ሞዴል ጽሑፍ ይቀርብላቸዋል፡፡ በሞዴል ጽሑፉ አደረጃጀት መሰረት የራሳቸውን ሀሳብ ያደራጃሉ፡፡ በመጨረሻም፣ የራሳቸውን ክሂልና የዓረፍተነገር አወቃቀር ተጠቅመው ይጽፋሉ፡፡ ሌላው ዘውግ ተኮር አቀራረብ (Genre approach) ከውጤት ተኮር አቀራረብ የመነጨ ቢሆንም ጽሑፉ በተፈጠረበት አውድ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ የጽሕፈት አቀራረብ ባህላዊና ማህበራዊ ልማዶችን ከግምት ውስጥ ያስገባና ጽሑፉ ከተጻፈበት ማህበራዊ አውድና ማህበራዊ ዲስኮርስ ስምምነቶች አኳያ የሚቀርብ ነው ( Djouambi and Razaiki, 2021; Baghzou, 2014; salvaraj & Aziz, 2019)፡፡ በዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ወደመጻፍ ተግባር ከመግባታቸው በፊት የሚጽፉትን ቴክስት ዘውግ/ዘር/ ማጥናት አለባቸው (Baghzou, 2014)፡፡ ለምሳሌ፣ የስራ ደብዳቤ እንዲጽፉ ከተፈለገ በቅድሚያ ሞዴል የስራ ደብዳቤ ማየት አለባቸው፡፡ የጋዜጣ ጽሑፍ የሚጽፉ ከሆነ ደግሞ ተጨባጭ መረጃዎች

እንዴት እንደሚፈለጉ የሚረዱ ምሳሌዎችን መመልከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሶስተኛው የመጻፍ አቀራረብ ሂደተ- ዘውግ ሲሆን በsalvaraj እና Aziz (2019) የተጠቀሱት (Rhalmi, 2018) እንደገለጹት ሂደተ-ዘውግ አቀራረብ ሌሎች የመጻፍ አቀራረቦችን አቀናጅቶ የያዘ ነው፡፡ የጽሑፍ ሂደቶችን ከሂደት ተኮር አቀራረብ፣ የጽሑፍን አላማና ማህበራዊ እውቀት ከዘውግ ተኮር አቀራረብ እንዲሁም የጽሑፍን ገጽታዎች ከውጤት ተኮር አቀራረብ ይይዛል፡፡ አራተኛ፣ ሂደት ተኮር አቀራረብ (process approach) ሲሆን፣ መጻፍ ሂደታዊና የተለያዩ ደረጃዎችን በማለፍ የሚከናወን ልምምዳዊ ተግባር መሆኑን Flower እና Hayes (1981) ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በክፍል ውስጥ ሂደት ተኮር አቀራረብ ትልቅ ትኩረት እያገኘ የመጣ አቀራረብ ሲሆን፣ ተማሪዎቸ በመጻፍ ሂደት የተለያዩ ሂደቶችን እንዲተገብሩ የሚያስገድድ ነው፡፡ Kroll (2001) መጻፍ በቀጥተኛ መስመር የሚከናወን ሳይሆን፣ ሂደታዊ በሆነ መልኩ የማቀድ፣ የማርቀቅ፣ የመከለስ፣ የማረምና የማተም ደረጃዎች ያሉት ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ሂደታዊና ተከታታይ ሲሆን፣ መምህራን የተማሪዎችን ጽሑፍ በማንበብ ምላሽ የሚሰጡበት እንደሆነም ተገልጿል፡፡ ከዚህ አኳያም በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ሂደታዊ የመጻፍ አቀራረብ ነው፡፡

የመጻፍ ክሂል ለመማር በጣም ውስብስብ እንደሆነ ሁሉ ለመመዘንም አስቸጋሪ መሆኑን Nodoushan (2014) ይገልጻሉ፡፡ ይሁንና የመጻፍ ፈተናን ለመመዘን ሁለት አይነት መስፈርቶች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህም አጠቃላይ መስፈርት (Holistic rubrics) እና ተንታኝ መስፈርት ( analytic rubric) ናቸው፡፡ አጠቃላይ መስፈርት መምህራንና ውጤት ሰጪዎች ከጽሑፉ ንዑሳን ክፍሎች ይልቅ በአጠቃላይ ጽሑፉ ላይ በማተኮር ቀድሞ ከተቀመጡ ባህሪዎች አኳያ የተማሪዎችን የጽሑፍ ደረጃ ለመለካት የሚጠቀሙበት መስፈርት ነው (Beyreli & Ari, 2009)፡፡ በሌላ በኩል ተንታኝ መስፈርት (analytic rubric) በተማሪዎች የጽሑፍ ስራ ውስጥ ያሉ ንዑሳን ክሂሎችን ለመመዘን ያስችላል፡፡ ይህ መስፈርት አንድን ጽሑፍ በነጠላ ውጤት ከመግለጽ ይልቅ በንዑስ በንዑስ ክሂል በመለያየት ለእያንዳንዱ ክፍል ውጤት በመስጠት ላይ ያተኩራል (Beyreli & Ari, 2009; Nodoushan, 2104)፡፡ ተንታኝ (ዘርዛሪ) መስፈርት ሙሉውን ጽሑፍ ባስገኙት ዝርዝር ክፍሎች (ዓረፍተነገር፣ ርዕስ፣ ሰዋስው፣ቃላት…) ላይ አጽንኦት በመስጠት የጽሑፉን ድክመቶች በቀጥታ ለይቶ በማመልከት ግልጽ የሆነ የማስተካከያ ግብረመልስ ለመስጠት እድል ይሰጣል፡፡ በዚህ ጥናትም በሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ መሰረት የተማሪዎች የመጻፍ ፈተናዎች የታረሙት ተንታኝ የጽሑፍ መገምገሚያ መስፈርትን በመጠቀም ነው፡፡

## 2.4.የመጻፍ ተነሳሽነት

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የተፈተሸው ጉዳይ የመጻፍ ተነሳሽነት ነው፡፡ ቋንቋን ለመማርና ስኬትን ለመወሰን ተነሳሽነት ጠንካራ ኃይል ነው፡፡ ተነሳሽነት እንደቀስቃሽ ኃይል በመሆን የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል በማሳደግ ትርጉም ባለው መንገድ እንዲጽፉ ያደርጋል (Hamidun & Hizwari, 2019)፡፡ በቋንቋ

ትምህርት ተነሳሽነት ተማሪዎች ወደተግባር እንዲገቡና በተግባሩ ላይ ምን ያህል ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው እንዲወስኑ የሚረዳ ወሳኝ ኃይል መሆኑን Agustinningsih & Andriani (2021) ገልጸዋል፡፡ Reid (2007)ን ጠቅሰው shumow and Chea (2015) ተነሳሽነት ለተማሪዎች መማር ያለውን አስፈላጊነት ሲገልጹ መኪና ያለነዳጅ እንደማይቀሳቀስ ሁሉ ተማሪዎችም ያለተነሳሽነት መማር አይችሉም ፡፡

ተነሳሽነት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ወደመጻፍ ተግባር እንዲገቡና አላማቸውን ለማሳካት ምን ያህል ጊዜ ተግተው መስራት እንዳለባቸው እንዲወስኑ የሚያደርግ ወሳኝ ኃይል ነው፡፡ በስነልቦና የትምህርት መስክ የተሰማሩ መምህራንና ጸሐፊዎች በቋንቋ ትምህርት ስኬታማ ለመሆን ተሳሽነት ቅድመሁኔታ እንደሆነ ይስማማሉ፤ በዚህም ግብረመልስና ተነሳሽነት የተማሪዎችን የቋንቋ መማር መሻሻል የሚቆጣጠሩ እሳቤዎች (perceptions) መሆናቸውን Agustiningsih እና Andriani (2021) ያስረዳሉ፡፡ ተነሳሽነት ከማንኛውም ተግባር ስኬት ጀርባ ያለ ወሳኝ ኃይል እንደሆነ የገለጹት ደግሞ Djouamb እና Rezaiki (2021) ናቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ተወዳዳሪ በመሆን ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ በሚል ውስጣዊ ተነሳሽነት ወይም ውጤት ለማግኘትና ቅጣትን ለማስወገድ በሚል ውጫዊ ተነሳሽነት አንድን ስራ ያከናውናሉ፡፡ Khosravi እና ሌሎች (2017) እንዳብራሩት ስለመማር ስልቶች ጥሩ ግንዛቤ መኖር ተማሪዎች ደስተኛ ሆነውና ተነሳስተው እንዲማሩ ሲረዳ፣ ተስማሚ የመማር ስልቶች አለመኖር ግን ተማሪዎች ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም፣ መምህራን የሚከተሉት የመጻፍ ማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ተነሳስተው እንዲጽፉ ወይም ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻሉ በተጨማሪ፣ ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚረዳ ትምህርታዊ ተግባር መሆኑን Duijnhouwer እና ሌሎች (2010) ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ Brown (2004)ን ጠቅሰው Duijnhouwer እና ሌሎች (2010) እንዳብራሩት ግብረመልስ የተማሪዎችን አዕምሯዊና ባህሪያዊ ተነሳሽነት ለማሻሻል ከተወሰኑ ጉዳዮች አንጻር መረጃ ይሰጣል፡፡ ግብረመልስ ግብን ለማሳካት፣ አዳዲስ ክሂሎችን ለማጎልበትና አዳዲስ አውዶችን ለማወቅ በሚል ውስጣዊ ተነሳሽነትን ወይም ውጤት ለማግኘት፣ ሽልማት ለመቀበልና በሌሎች ዘንድ ታዋቂ ለመሆን በሚል ውጫዊ ተነሳሽነትን ያስገኛል (Agricola et al., 2019)፡፡ በቀደመ ስኬታቸው ላይ የሚሰጣቸው ግብረመልስ በቀጣይ በሚኖራቸው ተነሳሽነት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ የጎላ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹በዚህ ላይ ጎበዝ ነህ/ነሽ›› (ችሎታን)፣ ‹‹ይህን ጠንክረህ/ሽ ሰርተኻል/ሻል›› (ጥረትን) የሚገልጽ ግብረመልስ ጠንካራ ግለብቃትና ተነሳሽነት እንዲኖር ያደርጋል (Shunk, 1995)፡፡ በሌላ በኩል፣ ተማሪዎች ለመጻፍ ተነሳሽነት የማይኖራቸው ከመምህሮቻቸው ተገቢ የሆነ ግብረመልስ ስለማያገኙ እንደሆነ Zahida እና ሌሎች (2014) ገልጸዋል፡፡ መምህራን የሚሰጡት ግብረመልስ ግልጽነት የጎደለውና ጠቃሚ በማይሆንበትም ጊዜ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ይቀንሰዋል፤ለመጻፍ እንዲፈሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም፣ ገንቢ

ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት በመጨመር ረገድ ከፍ ያለ ሚና ይጫወታል፡፡

በአጠቃላይ፣ በዚህ ክፍል የመጻፍ ምንነት፣ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች እንዲሁም የግብረመልስ ምንነት፣ አይነቶችና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጻፍ ተነሳሽነት ምንነትና ከግብረመልስ ጋር ያላቸው ትስስር ተዳሷል፡፡ የግብረመልስ አይነቶች በመጻፍ ክሂል፣ ግለብቃት ዕምነትና ተነሳሽነት ላይ ያላቸው ግንኙነት ተገልጿል፡፡ በመሆኑም፣ ጥናቱ የሚያተኩረው በእነዚህ መሰረታዊ ጽንሰሀሳቦች ግንኙነት ላይ ነው፡፡

## 2.5.የተዛማጅ ቀደምት ጥናቶች ክለሳ

ግብረመልስ በመጻፍ ክሂል፣ በመጻፍ ተነሳሽነት፣ በመጻፍ አመለካከት ወዘተ. ላይ ያለው ተጽዕኖ፣ በግብረመልስ አይነቶችና ተያያዥ ሀሳቦች ላይ በውጪ ሀገር የተሰሩ በጣም በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም፣ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው የተወሰኑ ጥናቶች በአጭሩ ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡ Hao እና Razali (2022) የጥንድ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ግለብቃት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመፈተሽ ከፊል ሙከራዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው የጥንድ ግብረመልስ የተማሪዎችን ጽሑፍ ይዘት፣ አደረጃጀትና ሰዋስው እንዲሁም የመጻፍ ግለብቃታቸውን አሻሽሏል፡፡ Agustiningsih እና Andriani (2021) የጽሑፍና የቃል ቀጥተኛ የማስተካከያ ግብረመልስ በተማሪዎች የጽሑፍ አፈጻጸም (ብቃት) እና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ አጥንተዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ሲሆን፣ ቀጥተኛ የቃልና የጽሑፍ ማስተካከያ ግብረመልስ በተማሪዎች የጽሑፍ አፈጻጸምና ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው የጥናት ውጤቱ አመልክቷል፡፡ Ismail እና ሌሎች (2014) በበኩላቸው የመምህራን ግብረመልስ (የቅርጽና የይዘት) በተማሪዎች የመጻፍ አፈጻጸም ላይ ያለውን ተጽዕኖ አጥንተው ግብረመልስ የተማሪዎችን ጽሑፍና የወደፊት ትምህርት እንደሚያሻሽል አረጋግጠዋለ፡፡ Sobhani እና Tayebipour (2015) የቃል ግብረመልስ (ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ) እና የጽሑፍ ግብረመልስ (ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ) በተማሪዎች የድርሰት ጽሑፍ ላይ ተጽዕኖ የቃል ግብረመልስ (ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ)፣ የጽሑፍ ግብረመልስ (ቀጥተኛ ብቻ) አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ cui እና ሌሎች (2021) ፣ Zahida እና ሌሎች (2014)፣ Hamidun እና ሌሎች (2013) እና Rahmawati (2015) ግብረመልስ (የጥንድ፣ የጽሑፍ፣ የቃል፣ ይዘት ተኮር… ግብረመልሶች) በተማሪዎች የጽሑፍ ጥናት፣ ውጤት፣ ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳላው አሳይተዋል፡፡ Agricola (2019) የግብረመልስ መጠየቂያ ቅጽና የመምህር ግብረመልስ በተማሪዎች የግብረመልስ አረዳድ፣ ግለብቃትና ተነሳሽነት ላያ ያላቸውን ተፅዕኖ ፈትሸዋል፡፡ የቃል ግብረመልስ ከጽሑፍ ግብረመልስ ይልቅ በተማሪዎች የግብረመልስ ግንዛቤ፣ የጽሑፍ ጥራትና ብዛት ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ታይቷል፡፡ ነገርግን የተማሪዎችን ግለብቃትና ተነሳሽነት እንደማያሻሽል ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በአንጻሩ Whalley እና Fetham (1994) የተለያዩ

ግብረመልሶች በአራት ቡድኖች የመጻፍ ክሂል ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ አጥንተው ምንም ግብረመልስ ያልተሠጣቸው ቡድኖችም ሳይቀሩ የድህረ ትምህርት የጽሕፈት ክሂላቸው ተሻሽሏል፡፡ በዚህም የመምህራን ግብረመልስ በጽሑፍ ክሂል ላይ ምንም ተጽዕኖ የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ በመሆኑም፣ በአንድ በኩል ግብረመልስ በመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው የሚገልጹ ጥናቶች መኖራቸው በሌላ በኩል ደግሞ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው የሚገልጹ የጥናት ውጤቶች መገኘታቸው ተጨማሪ ጥናት መካሄድ እንዳለበት ያመለክታሉ፡፡

## 3.የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በባህሪው መጠናዊ ምርምር ሲሆን ባለአራት ቡድን ከፊል-ፍትነታዊ (quasi-experiment) የጥናት ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ የጥናቱን ተሳታፊዎች የሙከራና የቁጥጥር ቡድን በማድረግ ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና በመፈተንና የተነሳሽነት መጠይቆችን በማስሞላት የተከናወነ ነው፡፡ የጥናቱ ነጻ ተላውጦ ሶስት ግብረመልስ ዘርፎች (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ ግብረመልሶች) ያሉት ሲሆን ጥገኛ ተላውጦዎቹ ደግሞ የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ናቸው፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በሐይቅ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኝ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ ይህ የጥናት አካባቢ በዓላማ ተኮር ዘዴ የተመረጠ ሲሆን፣ በዚህ ስልት የተመረጠበት ዋነኛው ምክንያት የመምህራንን ቀና ትብብር ለማግኘት ብቻ ሳይሆንን ለጥናቱ በቂ የሆነ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት የሚገኝበት ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ በከተማ አስተዳደሩ ስር ኹለት አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ሐይቅ ቁጥር አንድና ሐይቅ ቁጥር ኹለት) የሚገኙ ሲሆን፣ ሐይቅ ቁጥር አንድ ትምህርት ቤት በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል የሚያስተምር ቢሆንም፣ ከ5ኛ-8ኛ ያለው እርከን በአላማ ተኮር ዘዴ ተመርጧል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከ5ኛ-8ኛ እርከን ያሉ የክፍል ደረጃዎች ከዓረፍተነገር በላይ በአንቀጽና በድርሰት ደረጃ ሰፋ ያሉ ጽሑፎች የሚጽፉባቸው የክፍል ደረጃዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ከእነዚህ የክፍል ደረጃዎች መካከል 7ኛ ክፍል በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በመሆኑም፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2016 ዓ.ም በሐይቅ ቁጥር አንድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ 144 የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በ7ኛ ክፍል ያሉት አራት የመማሪያ ክፍሎች ቅድመ ሙከራ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነው ተመጣጣኝ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ሶስቱን የመማሪያ ክፍሎች የሙከራ ቡድን (7ኛ A= 35 ፣ 7ኛ B = 36 ፣ 7ኛ C= 37 በድምሩ 108) እና የቁጥጥር ቡድን (7ኛ D = 36) ሆነው ተደልድለዋል፡፡

## 3.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ የግብረመልስ ምርጫዎች በተማሪዎች የመጻፍ ውጤትና ተነሳሽነት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመፈተሽ በዋናነት ኹለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም የመጻፍ ክሂል መለኪያ ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.1.1.የመጻፍ ክሂል መለኪያ ፈተና

የመጻፍ ክሂል መለኪያ ፈተና በዋናነት የተለያዩ ግብረመልስ ምርጫዎች በተማሪዎች የመጻፍ ውጤት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ለመመርመር የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በውስጡ የቅድመ-ትምህርትና የድህረ-ትምህርት የመጻፍ ፈተናዎችን የያዘ ነው፡፡ ዋና አላማውም ከትምህርት በፊትና ከትምህርት በኋላ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለመለካት ነው፡፡ የመጀመሪያው የመጻፍ ክሂል ፈተና ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ፈተና ( writing pre-test) ሲሆን፣ ይህ የመጻፍ ክሂል ፈተና ኹለቱም ቡድኖች (የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች) በጥናቱ ውስጥ በተለዩት የግብረመልስ አይነቶች ድጋፍ ሳይደረግላቸው ያላቸውን የመጻፍ ክሂል ለማወቅ የሚያስችል ፈተና ነው፡፡ በዚህም የኹለቱም (የሙከራና የቁጥጥር) ቡድን ተማሪዎች በተሰጡ የመጻፊያ ርዕሶች በተራኪ፣ በአስረጅና በአመዛዛኝ ስልቶች በእያንዳንዳቸው አንድ አንድ በድምሩ ሶስት ድርሰቶችን በቅድመ ፈተና ጽፈዋል፡፡

ኹለተኛው ፈተና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና (writing post-test) ሲሆን የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተለያዩ ግብረመልሶች (ቡድን አንድ የጽሑፍ፣ ቡድን ኹለት የቃልና ቡድን ሶስት የጥንድ) እየተሰጣቸው የተለያዩ ድርሰቶችን እየጻፉ ከተለማመዱ በኋላ የቀረበ ነው፡፡ የዚህ ፈተና መሰረታዊ አላማ የሙከራ ቡድኑን ከቁጥጥር ቡድኑ ጋር በማነጻጸር የተለያዩ ግብረመልሶች በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር አለማሳደራቸውን ለመፈተሽ ነው፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተና ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠ ሲሆን፣ አተገባበሩም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በጥናቱ በተገለጹት የግብረመልስ አይነቶች ተደጋጋሚ እገዛ እየተደረገላቸው መጻፍን በሂደታዊ አቀራረብ ከተለማመዱና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ጽሑፍ ደግሞ በተለመደው ዘዴ ምንም ማስተካከያ ሳይጻፍበት ታርሞና ውጤት ተሞልቶ እየተመለሰላቸው ከጻፉ በኋላ ነው፡፡ በድህረ ትምህርት የጽሑፍ ፈተና ተማሪዎች በተራኪ፣ በአስረጅና በአመዛዛኝ ስልት በእያንዳንዱ አንድ አንድ ድርሰት በድምሩ ሶስት ድርሰቶችን እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ አተገባበር ቅደምተከተል፣ የጻፉባቸው ጭብጦች፣ የመጻፊያ ስልቶቹና የተሰጣቸው ሰዓት ሁሉ ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች ተመሳሳይ ነው፡፡

### 3.1.2.የመጻፍ ክሂል መለኪያ ፈተናዎች አዘገጃጀት

ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተናዎቹ የተማሪዎችን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተራኪ፣ በአስረጅና በአመዛዛኝ ድርሰት የመጻፊያ ስልቶች የመጻፍ ተግባርን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ የቴክስት መጻፊያ ስልቶች የተመረጡት ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች የመጻፍ ተግባር ተመራጭ ናቸው ተብለው በአዲሱ አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ተማሪዎች አንቀጽ እንዲጽፉባቸው የቀረቡ ስልቶች ስለሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ስልቶቹ የተመረጡበት ምክንያት ከ5ኛ-8ኛ ክፍል አዲስ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምንባቦች የተጻፉባቸውና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መጻፍን የሚለማመዱባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተራኪ፣ በአስረጅና በአመዛዛኝ ድርሰት የመጻፊያ ስልቶች በእያንዳንዳቸው በቅድመ ትምህርት አንድ አንድ እንዲሁም በድህረትምህርት አንድ አንድ በድምሩ በቅድመ ትምህርት ሶስት በድህረ ትምህርት ሶስት በአጠቃላይ ስድስት የተለያዩ ጽሑፎችን እንዲጽፉ የሚያስችሉ የመጻፍ ተግባራት በአጥኚው ተዘጋጅተው በቋንቋ ባለሙያዎች ተገቢነታቸው ተረጋግጦ ለተማሪዎች ቀርበዋል፡፡

ለቅድመም ሆነ ለድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና የቀረቡት የመጻፊያ ርዕሶች በተራኪ ድርሰት፣ በአስረጅ ድርሰትና በአመዛዛኝ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችሉ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በተራኪ ድርሰት የሕይወት ታሪክ መጻፍ፣ ጅምር አንቀጽ መጨረስ፣ ከራስ ገጠመኝ ተነስቶ ተራኪ ድርሰት መጻፍ ናቸው፡፡ በአስረጂ ድርሰት ደግሞ የደን መጨፍጨፍ መንስዔና የሚያስከትለው ጉዳት፣ በመንግስት ትምህርት ቤት ከመማርና በግል ትምህርት ቤት ከመማር የቱ ይሻላል? ሰዎች ለምን ይሰደዳሉ? የሚደርስባቸው ጉዳት ምንድን ነው? ሱስና መዘዙ፣ የድፎ ዳቦ አገጋገር ሂደት፣ እንዲሁም፣ በአመዛዛኝ ድርሰት የቤተሰብ ምጣኔ ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? ለለማኝ/ ለኔ ብጤ መስጠት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? ተማሪዎች ቴሌቪዥን ማየት አለባቸው/ ማየት የለባቸውም? ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ሥራ ይበዛባቸዋል፤ የሚሉት የመጻፊያ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ለቅድመና ለድህረ ትምህርት የተሰጡት የመጻፍ ተግባራት የክፍል ደረጃውን በሚያስተምሩ፣ በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ በሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን በማስገምገም የክብደት/የቅለት ደረጃ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና ዳራዊ እውቀት አኳያ ተገምግመው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡

### 3.1.3.የጽሑፍ ክሂል ፈተና አስተራረም

ተማሪዎች በተራኪ፣ በአስረጅና በአመዛዛኝ የጽሑፍ ስልቶች የጻፏቸው ድርሰቶች እያንዳንዳቸው ለየራሳቸው በተዘጋጁ ዝርዝር መስፈርቶች ታርመዋል፡፡ በዚህም ለተራኪ ድርሰት አንባቢ፣ የሐሳብ አደረጃጀት (መነሻ፣መካከል፣ መጨረሻ)፣ ገፀባህሪያና መቼት፣ የቃላት አጠቃቀም እና የዓረፍተነገር አወቃቀር፣ የአንቀጽ አደረጃጀትና ተያያዥነት፣ የፊደል ግድፈትና ስርዓተነጥብ፣ ለአስረጅ ድርሰት ደግሞ የሀሳብ አደረጃጀትና ዕድገት (ርዕስና የሀሳብ ፍሰት)፣ ማብራሪያና ዝርዝር

ሀሳቦች፣ የቋንቋ አጠቃቀም (ሰዋስውና፣ የጽሕፍት ስምምነቶች)፣ ስርዓተነጥብና የፊደል እንዲሁም ለአመዛዛኝ ድርሰት የመግቢያ ዓረፍተነገር/አንቀጽና ደጋፊ ዓረፍተነገሮች/አንቀጾች አጻጻፍ (የምክንያትና ማስረጃ ሀሳብ አቀራረብ)፣ ማጠቃለያ ዓረፍተነገር/አንቀጽ አጻጻፍ፣ የቋንቋ አጠቃቀም/ሰዋስውና ቃላት፣ ፊደልና ስርዓተነጥብ ግድፈት በመስፈርትነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን፣ ሁሉም መስፈርቶች ከ1-3 ውጤት ይዘዋል፡፡ እነዚህ መስፈርቶች universidad de Murcia (2020-21) እና national assessment program–literacy & numeracy (2022) ያዘጋጁትን የጽሑፍ መገምገሚያ መስፈርት በመተርጎምና በማሻሻል የተሰወዱ ናቸው፡፡ የተማሪዎቹ ጽሑፎች ለዚሁ ጥናት አላማ በሰለጠኑ፣ የማስተርስ ድግሪ ባላቸውና ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ኮሌጅ ድረስ ረጅም የማስተማር ልምድ ባላቸው ሁለት መምህራን ታርመው ሁለቱም መምህራን የሰጡት ውጤት ለተራኪ ድርሰት ከ18% (6 መስፈርቶች በ3 ነጥብ ተባዝተው) ለአስረጅ ድርሰት ከ15% (5 መስፈርቶች በሶስት ነጥብ) እንደዚሁም ለአመዛዛኝ ድርሰት ከ15% (5 መስፈርቶች በ3 ነጥብ ተባዝተው) ተሞልቷል፡፡ የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች በኹለት አራሚዎች መካከል ያላቸው አስተማማኝነት (Inter-rater reliability) በፒርሰን ተዛምዶ የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ ተሰልቶ በቅድመሙከራ .903 ሲሆን፣ በድህረሙከራ ደግሞ .901 ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 3.1.4.የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ

የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያየጽሑፍ መጠይቅ በቅድመና በድህረ ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመመርመር ተግባር ላይ የዋለ ነው፡፡ መጠይቁ Payne (2012) የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመለካት የተጠቀሙበትን በመተርጎምና በማሻሻል የተወሰደ ነው፡፡ መጠይቁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በአጥኚው አማካሪዎች ተገምግሞ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የተነሳሽነት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁ 20 ዝግ ጥያቄዎች የያዘ ሲሆን፣ በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ መወሰን አልችልም (3) አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም (1) የሚል የመልስ መወሰኛ ስኬል አላቸው፡፡ የጥያቄዎቹ አስተማማኝነት ደረጃ በአልፋ ክሮንባኽ ተፈትሾ በቅድመትምህርት 0.75 እንዲሁም በድህረትምህርት 0.77 ያህል አስተማማኝ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

## 3.1.5.የጥናቱ አተገባበር ሂደት

የመጻፊያ ተግባራቱ ለተማሪዎች ከመቅረባቸው አስቀድሞ የክፍል ደረጃውን በሚያስተምሩ መምህራን እና መማሪያ መጽሐፉን ባዘጋጁት መምህራን ተገምግመው የተወሱ ማስተካከያዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሰረት 20 የመጻፊያ ርዕሶች በክፍል ውስጥ ቀርበው ነበር፡፡ ይሁንና ሁለቱ ርዕሶች ማለትም ‹‹ስለራሳችሁ ወይም ስለጓደኛችሁ የልደት በዓል አከባበር ሂደት ድርሰት ጻፉ›› የሚለው ርዕስ ከሃይማኖት አኳያ ልደት የማያከብሩ ሙስሊም ተማሪዎች በመኖራቸው እንዲሁም ‹‹ስኬታማ ሰው ለመሆን ጠንክሮ መስራት እንጂ እድል

አያስፈልግም›› የሚለው ሀሳብ ከተማሪዎች የእውቀት ደረጃ አንጻር ይከብዳል ከሚል አስተያየት በመነሳት ተግባር ላይ አልዋሉም፡፡ ስለሆነም 12ቱ የመጻፊያ ርዕሶች ለክፍል ውስጥ መለማመጃ የዋሉ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስድስት ርዕሶች ለቅድመና ለድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በመቀጠል የመጻፍ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ ለሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ስለየጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ ግብረመልስ ምንነትና አተገባበር እንዲሁም ስለመጻፍ ሂደቶችና ስለመጻፊያ ስልቶች ለኹለት ቀን ያህል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህ ከተከናወነ በኋላ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ልምምዱ ከጥቅምት 26/ 2016 እስከ ጥር 15/2016 ለሁለት ወር ከአስራ አምስት ቀን (ለ10 ሳምንታት) ተካሂዷል፡፡ በመጻፍ ልምምዱ ሂደት ለቡድን አንድ ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት በማንበብ በመገምገሚያ መስፈርቶቹ አማካይነት በማስመር፣ በማክበብና አስተካክሎ በመጻፍ ግብረመልስ ተሰጥቷል፡፡ ለቡድን ሁለት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የታዩ ስህተቶች ልቅም አድርጎ በማውጣት በክፍል ውስጥ ከክፍሉ ተማሪዎች አልፎ አልፎም ከተናጠል ተማሪዎች ጋር ቃላዊ ውይይት ተደርጓል፡፡ የቡድን ሶስት ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ በማቧደን (ጥሩ የሚጽፉትን ጥሩ ከማይጽፉት ጋር በማቀናጀት) መስፈርቶችን አባዝቶ በመስጠት አንዱ ለሌላው ጽሑፍ ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ ለቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ግን፣ ተመሳሳይ ርዕስ እየተሰጣቸው የጻፉትን ሰብስቦ ምንም አይነት ማስተካከያ ሳይጻፍበት ውጤት በመስጠት ብቻ ተመልሶላቸዋል፡፡ በዚህም በሙከራ ጥናቱ ወቅት በክፍል ውስጥ በመገኘት ስለመጻፍ ትግበራና ስለግብረመልስ አሰጣጥ ሂደት ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በመጨረሻም፣ የድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና በመፈተንና የተነሳሽነት መጠይቁን በማስሞላት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

## 4.የመረጃ ትንተና

ከመጻፍ ክሂል ፈተናና ከጽሑፍ መጠይቆች በቅድመና ድህረሙከራ የተገኙት መረጃዎች በገላጭና በትንበያዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ በዚህም ነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ሁሉንም መረጃዎች ስታትስቲካዊ በሆነ መንገድ ለመተንተን spss Vresion 23 ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በቅድሚያ የሁሉም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል በነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ ተፈትሾ ውጤቱ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 1 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1. የተማሪዎች የቅድመትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና በነጠላ ናሙና ልይይት (One way Anova)

| ቡድኖች | ናሙና | አማካይ ውጤት(ave.) | መደበኛ ልይይት(sd) | የነጻነት ደረጃ (df) | የልይይት ዋጋ(F) | የጉልህነት ደረጃ(Sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን 1 | 35 | 26.08 | 4.12 | 3<br>140 | 1.72 | .164 |
| ቡድን 2 | 36 | 25.06 | 3.95 | | | |
| ቡድን 3 | 37 | 24.71 | 2.90 | | | |
| ቡድን 4 | 36 | 26.65 | 5.14 | | | |

ከሰንጠረዥ 1 መረዳት እንደሚቻለው በቡድኖች መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል አማካይ ውጤት ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል። ይህን የአማካይ ውጤት መቀራረብ ይበልጥ ለማረጋገጥ ነጠላ ነሙና ልይይት ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል ። በዚህም የተገኘው የF ዋጋ F(3,140) =1.72, P= .164 ሆኗል። የተገኘው የP ዋጋ (.164) ከባለሁለት ጫፍ የስህተት ይሁንታ 0.05 በልጦ መገኘቱ (P>0.05) በቡድኖች የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል መካከል ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል። ይህ ማለትም የሙከራ ቡድኖችና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመትምህርት የመጻፍ ክሂላቸው ተቀራራቢ ናቸው ማለት ነው።

በመቀጠልም የተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ተፈትሿል። በዚህም በቡድኖች መካከል የመጻፍ ተነሳሽነት ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 2 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 2. የተማሪዎች የቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት በነጠላ ናሙና ልይይት (One way Anova)

| ቡድኖች | ናሙና | አማካይ ውጤት (ave.) | መደበኛ ልይይት (sd) | የነጻነት ደረጃ (df) | የልይይት ዋጋ (F) | የጉልህነት ደረጃ (Sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን 1 | 35 | 62.1 | 13.4 | 3<br>140 | .072 | .975 |
| ቡድን 2 | 36 | 62.4 | 11.1 | | | |
| ቡድን 3 | 37 | 61.9 | 10.6 | | | |
| ቡድን 4 | 36 | 61.1 | 11.2 | | | |

በሰንጠረዥ 2 እንደተመለከተው ተማሪዎች ያላቸው የቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል። ይሁንና ይህ የተነሳሽነት መቀራረብ ጉልህ መሆኑና አለመሆኑ መረጋገጥ ስላለበት በቡድኖች መካከልና በቡድኖች ውስጥ ያለው የመጻፍ ተነሳሽነት በነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ ተፈትሾ

የተገኘው የF ዋጋ (3,140)= .072, P= .975 ነው፡፡ የPዋጋ (.975) ከባለሁለት ጫፍ የስህተት ይሁንታ 0.05 በልጦ (P> 0.05) ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም፣ በቡድኖች መካከል የመጻፍ ተነሳሽነት ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ቡድኖቹ በቅድመትምህርት ያላቸው የመጻፍ ተነሳሽነት ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 4.1.የድህረትምህርት መረጃ ትንተና

የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ተፅዕኖ አለው?›› የሚል ነው፡፡ በዚህም በቡድኖች የድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል መካከል ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለመፈተሽ መረጃው በነጠላ ናሙና ልይይት (one way anova) ተሰልቶ ውጤቱ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 3 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3. የተማሪዎች የድህረሙከራ የመጻፍ ክሂል ውጤት በነጠና ናሙና ልይይት (one way anona)

| ቡድኖች | ናሙና | አማካይ ውጤት (ave.) | መደበኛ ልይይት (sd) | የነጻነት ደረጃ (df) | የልይይት ዋጋ(F) | የጉልህነት ደረጃ (Sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን 1 | 35 | 30.35 | 6.4 | 3<br>140 | 13.9 | .000 |
| ቡድን 2 | 36 | 32.75 | 5.9 | | | |
| ቡድን 3 | 37 | 25.90 | 3.4 | | | |
| ቡድን 4 | 36 | 26.80 | 3.9 | | | |

ከሰንጠረዥ 3 መገንዘብ እንደተቻለው በቡድኖች የመጻፍ ክሂል አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ይህ ልዩነት ጉልህ መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ውጤቱ በነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ ተሰልቶ የተገኘው የF ዋጋ F(3,140)=13.9፣ P= .000 ነው፡፡ በዚህም የተገኘው የ Pዋጋ (.000) ከባለሁለት ጫፍ የስህተት ይሁንታ (0.05) አንሶ በመገኘቱ (P< 0.05) በቡድኖቹ የመጻፍ ክሂል ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ይሁን እንጂ ነጠላ ናሙና ልይይት በቡድኖች መካከል ልዩነት እንዳለ ቢጠቁምም የትኛው ቡድን የተሻለ የመጻፍ ክሂል አለው የሚለውን ለማወቅ የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር (comparison among means) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህን ለማከናወን ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል ውጤቱ በቱኬይ ፖስት ሆክ (tukey post hock) የመተንተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ በዚህም መሰረት የቃል ግብረመልስ ያገኙ ተማሪዎች (m=32.75, sd=5.9) የጽሑፍ ግብረመልስ ካገኙት ተማሪዎች (m= 30.35, sd=6.4)፣ የጥንድ ግብረመልስ ካገኙት (m=25.9፣ sd= 3.4) እና ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች (m= 26.8, sd=3.9) የበለጠ የመጻፍ ውጤታቸው ተሻሽሏል፡፡ በአንጻሩ፣ የጽሑፍ ግብረመልስ ያገኙ ተማሪዎችም የጥንድ

ግብረመልስ ካገኙትና ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በበለጠ ሁኔታ የመጻፍ ክሂላቸው መሻሻል አሳይቷል፡፡

ኹለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ አለው?›› የሚለው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ የቡድኖቹ የድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መረጃ በነጠላ ናሙና ልይይት (one way anova) ተሰልቶ ውጤቱ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4 የተማሪዎች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት በነጠላ ናሙና ልይይት ትንተና (one way anova)

| ቡድኖች | ናሙና N | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (sd) | የነጻነት ደረጃ (df) | የልይይት ዋጋ (F ) | የጉልህነት ደረጃ ባለሁለት ጫፍ (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን 1 | 35 | 70.4 | 10.5 | 3<br>140 | 8.0 | .000 |
| ቡድን 2 | 36 | 69.8 | 10.4 | | | |
| ቡድን 3 | 37 | 62.1 | 11.3 | | | |
| ቡድን 4 | 36 | 60.4 | 11.2 | | | |

ከሰንጠረዥ 4 መረዳት እንደተቻለው በአራቱም ቡድኖች የድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ ይህ የአማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ የቡድኖቹ አማካይ ውጤቶች በነጠላ ናሙና ልይይት ዘዴ (one way anova) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚህም የተገኘው የF (3,140) ዋጋ 8.0፣ P= .000 ሲሆን፣ የ P ዋጋ (.000) ከባለኹለት ጫፍ የስህተት ይሁንታ (.05) አንሶ በመገኘቱ (P<.05) በቡድኖች መካከል ጉልህ የሚባል ልዩነት እንዳለ ትንተናው ያመለክታል፡፡

የትኛው ቡድን የተሻለ የድህረ ሙከራ የመጻፍ ተነሳሽነት እንዳለው ለማወቅ የተገኙት መረጃዎች በአማካይ ውጤቶች ንጽጽር (multiple comparisons among means) ስልት በቱኪይ ፖስት ሆክ (tukey post hock) ተተንትኖ የጽሑፍ ግብረመልስ አማካይ (70.4) እና የቃል ግብረመልስ አማካይ (69.8) በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ በተቀራራቢ ደረጃ ጉልህ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ፣ ጥንድ ግብረመልስ በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ እንደሌለው ትንተናው አመላክቷል፡፡

## 5.የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ በመመርመር ላይ ያተኮረ እንደሆነ ቀደም ብሎ ተገልጿል፡፡ በቅድሚያ ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ተፅዕኖ

አለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የቡድኖቹ የቅድመትምህርት የመጻፍ ውጤት በነጠላ ናሙና ልይይት ተፈትሿል፡፡ የትንተና ውጤቱም (F (3,140)= .072, P= .975) በሁለቱ ቡድኖች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንደሌለ አሳይቷል፡ ፡ በመቀጠል ከትምህርት በኂላ የአራቱም ቡድኖች የድህረመጻፍ የመጻፍ ክሂል ውጤት በነጠላ ናሙና ልይይት ተፈትሾ የተገኘው ዋጋ F(3,140)=13.9፣ P= .000 ሲሆን፣ የተገኘው የ P ዋጋ (.000) ከ0.05 አንሶ (p<0.05) ተገኝቷል:: ልዩነት መኖሩ ከተረጋገጠ በኂላ የትኛው የግብረመልስ ምርጫ ከሌሎቹ የበለጠ ጉልህ ተጽዕኖ እንዳለው ለማወቅ ደግሞ ከአማካይ ውጤቶች ማነጻጸሪያ (multiple comparison among means) ዘዴዎች መካከል የቱኬይ ዘዴ (Tukey honesty test) ተግባራዊ ተደርጎ የቃል ግብረመልስ (አማካይ 32.75፣ መደበኛ ልይይት 5.9) እና የጽሑፍ ግብረመልስ (አማካይ 30.35፣ መደበኛ ልይይት 6.4) ከጥንድ ግብረመልስ (አማካይ 25.9፣ መደበኛ ልይይት 3.4) እንዲሁም፣ ከቁጥጥር ቡድኑ (አማካይ 26.8፣ መደበኛ ልይይት 3.9) የበለጠ የመጻፍ ክሂልን በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ይሁንና የቃል ግብረመልስ ከጽሑፍ ግብረመልስ ጋር ሲነጻጸር የበለጠ ጉልህ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው መረጃዎቹ አሳይተዋል፡፡ በዚህም የጽሑፍና የቃል ግብረመልሶች በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሲኖራቸው፣ የጥንድ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ምንም ተፅዕኖ እንደሌለው ተረጋግጧል፡፡ ይህም Agustiningsih እና Andriani (2021)፣ Sobhani እና Tayebipour (2015) እንዲሁም Rahmawati እና ሌሎች (2015) የቃልና የጽሑፍ ግብረመልስ በተማሪዎች ድርሰት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ አላቸው ከሚለው ጋር የሚስማማ ነው፡፡ በአንጻሩ የጥንድ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው ከሚለው የHao & Razali (2022) ጥናት ውጤት ጋር አይደጋገፍም፡፡

የኹለተኛው ጥያቄ ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ አለው? የሚል ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ በአራቱም ቡድኖች የቅድምትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መካከል ልዩነት እንደሌለ (F(3,140)= .072, P= .975, P>.05) ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም የቡድኖቹ የድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት በነጠላ ናሙና ልይይት ተፈትሾ የተገኘው ዋጋ F(3,140)=8.0 ፣ P= .000 ሲሆን፣ የተገኘው የP ዋጋ (.000) ከ0.05 አንሶ (p<0.05) ተገኝቷል:: ይህም በቡድኖች መካከል የመጻፍ ተነሳሽነት ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በዚህም የትኛው የግብረመልስ ዘዴ የበለጠ ተነሳሽነትን ያሻሽላል የሚለውን ለማወቅ ውጤቱ በቱኬይ ፖስት ሆክ ዘዴ የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር ተደርጓል፡፡ በዚህም የጽሑፍ ግብረ መልስ (አማካይ 70.4፣ መደበኛ ልይይት 10.5) እና የቃል ግብረመልስ (አማካይ ውጤት 69.8፣ መደበኛ ልይይት 10.4) በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ እኩል አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በዚህም የጽሑፍና የቃል ግብረመልስ የተሰጣቸው ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት እንደጨመረ መረጃዎቹ አመልክተዋል፡፡ ይህ ውጤት ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያሻሽላል ከሚለው የHamidun እና ሌሎች (2013) እና ከAgustiningsih እና Andriani (2021) ጥናት ውጤት ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ

በኩል የጥንድ ግብረመልስ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያሻሽላል ከሚለው የcui እና ሌሎች (2021) ጥናት ጋር ተደጋጋፊ አልሆነም፡፡

## 6.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የመምህራን የግብረመልስ ምርጫ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለማጥናት ታልሞ የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ኹለት ሲሆኑ የመጀመሪያው ጥያቄ ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ) በተማሪዎች የመጻፍ ውጤት ላይ ተፅዕኖ አለው? የሚል ነው፡፡ ኹለተኛው ጥያቄ ደግሞ ግብረመልስ (የጽሑፍ፣ የቃልና የጥንድ በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ አለው? የሚል ነበር፡፡ በጥናቱ 144 የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በአራት ቡድን ተመድበው ተሳትፈዋል፡፡ ጥናቱ ለሙከራ ቡድኖቹ የተለያዩ የግብረመልስ ምርጫዎችን በማቅረብ፣ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደው ዘዴ መጻፍን በማስተግበር ለ10 ሳምንት ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ንድፍን የተከተለ ሲሆን፣ ተጠኝዎችን በዕድል ሰጪ ናሙና ዘዴ በመምረጥና የሙከራና የቁጥጥር ቡድን በማድረግ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተናና በተነሳሽነት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡

ከተጠኝ ተማሪዎች ቅድመና ድህረትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተናና የተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በነጠላ ናሙና ልይይት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከመረጃ ትንተናዎቹ የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው ለተማሪዎች ድርሰት የሚሰጥ የጽሑፍና የቃል ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ውጤትና ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ በዚህም፣ መምህራን የተማሪዎችን ጽሑፍ ውጤት እየሰጡ ከማለፍ ይልቅ በሂደታዊ የመጻፍ አቀራረብ ተደጋጋሚ የጽሑፍና የቃል ግብረመልስ በመስጠት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ማሳደግ ይችላሉ የሚል አስተያየት ተጠቁሟል፡፡

**ማረጋገጫ**

ይህ ጥናት የአጥኚው የግል ስራ የሆነና ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነጻ ነው፡፡

ጥናቱ በጂማ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ ነው፡፡

# ዋቢዎች

ማረው አለሙ ። (1996)። በሳል ድርሰት ማስተማሪያ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ።

Adarkwah M.A. (2021). The power of assessment feedback in teaching and learning: a narrative review and synthesis of the literature. https://www.researchgate.net/publication/349915536.

Agricola B., Prins F.J. & Sluijsmans D.M (2020).Impact of feedback request forms and verbal feedback on higher education students' feedback perception, self-efficacy, and motivation. Published by Informa UK Limited, trading as Taylor & Francis Group. https://doi.org/ 10.1080/ 0969594X.2019.1688764.

Agustiningsih N & Andriani F. (2021). A Study On Direct Corrective Feedback In Improving Students' Writing Performance And Motivation. Vol. 2, No. 1.

Akkuzu N. (2014) Te Role of Different Types of Feedback in the Reciprocal Interaction of Teaching Performance and Self-efcacy Belief. *Australian Journal of Teacher Education, vol.39 (3)* http://ro.ecu.edu.au/ajte.

Zubaidi N. (2015). Sociocultural Theory. State University of Malang. https://www.researchgate.net /publication/277892662

Al- Zyoud A., Al-jamal D. & Baniabdelrahman A. A (2017) Mind Mapping and tudents' SWriting Performance: University–Jordan. Vol 8 no 4.19. https://www.researchgate.net/ publication/321859632.

Babni A. (2016) Teaching Writing: From Theory to Practice. International Journal of Science and Research (IJSR). Volume 7, Issue 10, www. nijsr.net.

Baghzou S. (2014). *A Model of Feedback Made on Students' Writing*: Case Study: "Second Year Student at the University Centre of Khenchela".

Barnard R. C. & Campbell L. (2005) Sociocultural Theory and the Teaching of Process Writing: The Scaffolding of Learning in a University Context.

Beyreli L. & Ari (2009) The Use of Analytic Rubric in the Assessment of Writing Performance -Inter-Rater Concordance Study.

Cui Y. S., *Schunn C. D. Gai, X., Jiang Y & Wang Z.* (2021) Effects of trained peer Vs teacher feedback on EFL students'writing performance, self efficacy & internalization of motivation. www.frontiersin.org. Volume 12, Article 78847

Daffern T. & Mackenzie N. M. (2020) Theoretical perspectives and strategies for teaching learning writing. : University of Camberra. https://www.researchgate.net/publication/ 342845063.

Driver M. (2021). Cognitive Theoretical Perspectives of Corrective Feedback. https://www.cambridge.org/core/terms.

Duijnhouwer H., Prins F J. & Stokking K. M. (2010). Feedback providing improvement strategies and reflection on feedback use: Effects on students' writing motivation, process, and performance. journal homepage: www.elsevier.com/locate/learninstruc

Eggleston B.(2017).Relationship between writing self efficacy and writing fluency in aperformance feedback. https://surface.syr.edu/thesis

Elashri I. (2013). The Impact of the Direct Teacher Feedback Strategy on the EFL Secondary Stage Students' Writing performance: Mansoura University.

Fathman A. k. & Whalley E. (1990) Teacher response to students' writing.Focus on form versus content.

Ferris D. (2003) Response To Students Writing.Implication For Second Language Students. Lawrence Erlbaum Associates, Publishers Mahwah, New Jersey.

Hamidun N., Hizwari S. & Othman N. F. (2013) Enhancing Students' Motivation by Providing Feedback on Writing: The Case of International Students from: International Journal of Social Science and Humanity,Vol.2,No.6.https://www.researchgate.net/publication/283781036

Hao H. & Razali A. B. (2022).The Impact of Peer Feedback on Chinese EFL Junior High School Students' Writing Performance.Faculty of Educational Studies. Published by Canadian Center of Science and Education. Vol. 15, No. 9.

Harmer J. (2001). How to teach English: ana introduction to the practice of English language.3rd ed. Printed in Malaysia.

Hattie J. & Timperley H. (2007) The Power of Feedback.Review of Educational Research March 2007, Vol. 77, No. 1.

Hyland K. & Hyland F. (2006) Feedback on second language students' writing. Printed in the United Kingdom, Cambridge University Press.

Kalipa Z. (2014).Teaching Strategies to Improve the Writing Skills for Grade 8 & 9 Learners in English First Additional Language: A Case Study of Four High Schools in the Cradock Education District

Ken C. (1990). Feedback in the writing process: A model & Method for implementation. *ELT Journal Volume 44/4,* https://www.researchgate.net/publication/220017610

Klimova, B. F. (2013). Approaches to the teaching of writing skills. International Conference on Education & Educational Psychology. . Published by Elsevier L.

Kluger A. N. & DeNisi Angelo ( 1996) The Effects of Feedback Interventions on Performance: A Historical Review, a Meta-Analysis, and a Preliminary Feedback Intervention Theory. American Psychological Association, Inc.

Kroll B (edt). (1990) Second language writing.Research insights for the classroom.Cambridge University pres.

Maryam K., Ghoorchael B & Mufrad A. A. (2017) The Relationship between Writing Strategies, Self-Efficacy and Writing Ability: A Case of Iranian EFL Students. Gorgan, Iran**.** Volume: 05 Issue: 03**.** (www.eltsjournal.org.

Meziane R. (2019). The Impact of Teachers' Feedback on Students' Writing Competence: The Case of 3rd Year EFL Students at TlemcenUniversity.

National assessment program –literacy & numeracy (2022). Writing Narrative markiNg guide: New South Wales, State of Western Australia

Nodoushan M. A (2014). Assessing Writing:A Review of the Main Trends. Iranian Institute for Encyclopaedia Research. *Volume 1, No. 2,*

Nurfaidah S. (2018). Vygotsky's Legacy on Teaching and Learning Writing as Social Process. Volume 4 No.2.

Panadero E. and Lipnevich A. (2021) A Review of Feedback Models and Theories: Descriptions, Definitions, and Conclusions.Volume 6. https://www.researchgate.net/ publication/ 357457774.

Panahi P., Birjandi P. and Azabdaftari B. (2013) Toward a sociocultural approach to feedback provision in L2 writing classrooms. http://www.languagetestingasia.com/content/3/1/13

Payne A. R. (2012). Development Of The Academic Writing Motivation Questionnaire. *A Thesis Submitted to the Graduate Faculty of The University of Georgia in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree*. Athens, Georgia.

Rahmawati E. D., Raja P. & Nurweni A. (2015). Student's Oral & written Feedback on students' writing Quality at one of pre intermediate writing class. *Online Published: November 2, 2015*

Razali R, & Jupri R (2016). Exploring Teacher Written Feedback and Student Revisions on ESL Students' Writing. Volume 19, Issue 5: *www.iosrjournals.org.*

Rietdijk, S., Weijen D. V., Janssen T. & Berg H. V. (2018).Teaching Writing in Primary Education: Classroom Practice, Time, Teachers' Beliefs and Skills. Journal of Educational Psychology. Advance online publication. http://dx.doi.org/10.1037/edu0000237.

Sarwat S., Ullah N., Anjum H. M., & Bhuttah T. M. (2021) Problems and Factors affecting students English writing skills at elementary level. Vol 20 (Issue 5), http://ilkogretim-online.org.

Schunk D. H.(2012).Learning Theories: An Educational Perspective.501 Boylston Street.6th Ed.

Selvaraj M. & Aziz A. A. (2019) Systematic Review: Approaches in Teaching Writing Skill in ESL Classrooms. International Journal of Academic research in progressive education & development. Vol. 8, No. 4, http://creativecommons.org/licences/by/4.0/legalcode.

Tillema M. (2012). Writing in first and second language. Empirical studies on text University Press.http:/www.lotschool.nl.

Toria G., Harbaugh A. G,, Shankland R. K. **&** Wolbers Kimberly (2012). Relation ship between writing motivation, writing activity and writing performance: Effects on grade, sex & ability. Springer Science + Business Media B.V. 2012. https:// www. researchgate.net /publication/ 257643274

Tsagari D. (2019) Interface between feedback, assessment and distance learning written assignments. Research Papers in Language Teaching and Learning Vol.10,No. 1, http://rpltl.eap.gr

Universidad de Murcia (2020-21) writing narrative marking guide. 280 Elizabeth Street Sydney NSW 2000.

Ur, P. (1996) A Course in Language Teaching; Practice and Theory: New York , Cambridge

Wahyuni Sri (2017).The Effect of Different Feedback on Writing Quality of College Students with Different Cognitive Styles. *Indonesia.* Volume 17 (1).

Zahida R., Farrah M. & Zaru N. (2013).The Impact of Three Types of Written Feedback on the Motivation and Writing Skill of English Major Students at Hebron University. *28*(5).